ከከበደ ሚካኤል።

# ብርሃነ ኅሊና።

NIGUSS
DIGITAL LIBRARY

ለልዑል መኰንን መስፍነ ሐረር
የተሰጠ ገጸ በረከት።

# ብርሃነ ኅሊና።

ለልዑል መኰንን መስፍነ ሐረር

የተሰጠ ገጸ በረከት።

ከልዑል መኰንን አሽከሮች አንዱ

ከበደ ሚካኤል ተጻፈ።

በግርማዊ ቀዳማዊ ኀይለ ሥላሴ ንጉሰ ነገሥት ዘኢትዮጵያ በ፴፫ኛው ዘመነ መንግሥት

አዲስ አበባ ፲፱፻፶፮ ዓ.ም

የከፋት መሠረት እንዲነቀል መርዙ ጎሊና ለማግኘት እንድከም በብዙ።

ይህንን መጽሐፍ
ያለ ደራሲው ፈቃድ ማሳተም ክልክል ነው።
COPYRIGHT

# ማውጫ።

መቅድም። 10
አንድ አምላክ። 11
የሰው ሐሳብ። 12
ዓለምና ጊዜ። 14
የሰው ዕድል። 17
የሰው ጠባይ። 19
የግፈኞች ፍርድ። 22
አባት ልጅ አህያ። 25
ደግነትና ክፋት። 28
ምሥጢርና ወሬ። 29
በዐመፃ የመጣ ገንዘብ። 32
የሀብት ትዕቢት። 33
የክፋት ተጋብኦነት። 34
ሁለት ወንዳማቾች። 35
ጥበብ። 38
ሰውና ታሪክ። 40
ሕይወት እንቅልፍ ነች። 42
ባልና ሚስት። 44
አንበሳና ጦጣ። 46
ሥራ። 47
ንግሥት አግሪፒና። 50
የሰማይ ጉዞ። 51
ሙሴ። 53
ትሕትና። 56
የተኛ ሰው። 57
የማይለወጡ ነገሮች። 59
ነፋስ ይዞት ሄደ። 61
መስከረም ጠባ። 62

አንቲስቴኔ።....63
ሊቅና ባልተኛ።....63
አሪስቶት።....64
ጥልቅ አሳቦች።....65
የደስታና የሐዘን ቅልቅልነት።....74
ሁለት መላጦች።....76
ለጸሓፊዎችና ለፈላስፎች ምስጋና።....77
ለእመቤታችን ምስጋና።....78
ጥልቅ አሳቦች።....80
አዳምና በሬው።....82
ስለደራሲው በጥቂቱ....83
የደራሲው ሥራዎች።....84

ወጣቱ መስፍን በድንገተኛ ሞት ከዚህ ዓለም ከተለዩ ካንድ፥ ዓመት በላይ ሆነ። ዳሩ ግን ሁላችንም በልባችን የምንመኝላቸው ረዥሙን ዕድሜ ስለ ነበረና የልዑልነታቸው እንዲህ ባጭር መቅረትበመንፈሳችን ውስጥ ጨርሶ ያልነበረ ነገር በመሆኑ የተፈጸመውን ነገር ስለ ልዑልነታቸው ከነበረን ምኞትና አሳብ ጋራ ልናገናኘው ባለመቻላችን አሁንም ቢሆን ብዙ ጊዜ የተለዩን መሆናቸውን እየረሳን በመካከላችን ያሉ ይመስለናል። የደረሰው ነገርና አሳባችን እስቲታረቁ ድረስ ብዙ ጊዜ ሳይፈጅብን አይቀርም።

ምንም እንኳ ልዑልነታቸው በሥጋዊ ሕይወት ከኛ የተለዩ ቢሆኑ ታሪካቸውና መታሰቢያቸው በኢትዮጵያ ሕዝብ ዘንድ ለዘለዓለም የማይረሳ ሆኖ ይሆራል። ለልዑልነታቸው ገጸ በረከት ሆና ተሰጥታ የነበረችው ይህች መጽሐፍ አሁን አራተኛ ጊዜ ታትማ በምትወጣበት ሰዓት ለታሪካቸው መታሰቢያ ሆነ ከሚኖሩት ካያሌ ነገሮች አንዷ ሆና ዜናቸውን እንድታስታውሰን ደራሲው ምኞቱን ይገልጣል።

የሐረሩ መስፍን መኰንን ተፈሪ
ባለመልካም ጠባይ ባለ መልካም ባሕሪ
ቸኵሎ የመጣ ያልታሰበ ጠሪ
በድንገት ወሰደው ቶሎ በቅጽበት
ከጃንሆይ ከእቴጌ ሳይሰናበት።
ሆኖበት ነው እንጂ ከቶ የማያልፈው
ቢቸኵል ነው እንጂ ጠሪ ቢያጣድፈው
አሽከሮች ሳይጠፉ ሎሌ ከቤት ሞልቶ
መስፍኑ የሄደው ብቻውን ተነሥቶ።
በውነት የሞተብን አንድ ሰው ከሆነ
ምነው አልቃሽ በዛ ፍጥረት ሁሉ አዘነ?
መርዶ አርጂ ነው አሉ ወሬ ያሳሳተ
ለካ ብዙ ሰው ነው ከሱ ጋር የሞተ።
የሐረር አውራጃ መልካሙን ገዥ፥ አታ፤
ድኻ ችግረኛ ከፉኛ ተቀጣ።
ለብዙ ነበረ የሚያገለግለው
እንግዲህ ያ ሁሉ አይዞኽ ባይ ጐደለው።
ስንቶች ተበተኑ ያላስታዋአሽ ቀሩ፤
ስንቱ ደጀ ጠኒ ተዘጋበት በሩ።
ሁሉም ሲል ሰማነው አጣን የሚረዳን፤
ውሸት እንደ ጃንሆይ ማንም አልተጐዳም።
ዐይናቸው ፊታቸው ትኵስ እንባ ለብሶ
ሲሉ ሰማናቸው ጃንሆይ በለቅሶ
እኔ ሞተ ስለው ሕያው እየሆነ
ሌት ተቀን ከፊቴ እየተደቀነ
አላሳርፍ አለኝ አሳጣኝ ጸጥታ፤
የምወደው ልጄ ሆነብኝ በሽታ።
ብፈልግ ባስፈልግ በየትም በየት

ሁሉም የለም፥ አሉኝ የልጅ መድኀኒት።
ሳወቀው ሁሉ እንጂ ለተመለከተው
መች ለጃንሆይ ብቻ መኰንን የሞተው።
ገንዘቡ ነበሩ ርኅራኄ ትሕትና፤
ይጣጣር ነነእብረ ለመልካሙ ዝና
ኸርምሩ በሞላ ሳለ መልካም ሆኖ
ሁሉን ትቶ ሄደ ወጥኖ ወጥኖ።
በረጅም ስናስብ ሁላችን በከንቱ
አያሳዝንም ወይ በኸምር መቅረቱ
አያሳዝንም ወይ በኸምር መቅረቱ።
መቼም አልታከተው መቼም አልደከመ፤
ይሟገት ነበረ ለሁሉ እየቆመ።
ለብዙ ሰው ነበር የዋለው ውለታ፤
አሁን በሱ ጊዜ ብቻውን ተረታ።
ከፍቶት ይሆንን ልቡ ተቀይሞ
ብቻውን የሄደ ከሰው ሁሉ ቀድሞ።
ዐቅም አነሰ እንጂ አጠረን ጉልበቱ፤
መች ይቀር ነበረ ሰው ሁሉ መርዳቱ
ሲፈርስ፥ እያየነው የመኰንን ቤቱ።
ከወደቀ ወዲያ እንደዩ ከፈረሰ
አይነሣም አሉ ዐፈር ከለበሰ።
ሲወድቅ እንደ ዘበት ሲፈርስ እንደ ዋዛ
አይነሣም ቤቱ ማዘኑም ቢበዛ።
ግርማዊ ጃንሆይም እንዲህ ይጥናኑ፤
ግርማዊት እቴጌም እንዲህ ይጥናኑ፤
ልዕልት ሣራ ግዛው እንግዲህ ይጣንኑ፤
የሚቻል አይደለም ከባድ ነው ማዘኑ።

## ልዑል ሆይ።

ይህች መጽሐፍ ገጸ በረከት አድርጌ ለልዑልነትዎ፥ ለመስጠት አስቤ የዠመርኩት የዛሬ ስድስት ዓመት ነበረ። አገራችን የጦር አደጋ ደርሶባት ልዑልነትዎ በስደት ምክንያት ወደ አውሮፓ ስለ ሄደ ዠምሬው የነበረውን በልዩ ልዩ ብስጭት ምክንያት ሁለት ዓመት ሙሉ ሳልቀጥል ተውኩት። በኋላ ግን የኢትዮጵያ ነጻነት ለመመለሱ ያለን ተስፋ እየተረጋገጠ ስለ ሄደ የዠመርኩትን እንደ ገና ለመቀጠል ሐሳቤ ተነሣሣ። ላሁኑ ሰዓት አድርሶኝ ልዑልነትዎ ከግርማዊ አባትዎ ከግርማዊ አባትዎ መንግሥት ለመመለስ በቅቶ ሐሳቤን ለመፈጸም የፈቀደልኝን ሕያው እግዚአብሔርን እያመሰገንኩ፤ ይህቺን ትንሽ መጽሐፍ ለልዑልነትዎ በረከት አድርጌ አቀርባለሁ።

ያራት ዓመት ድካም የተለፋበት

ልዑል ሆይ እንሆ ገጸ በረከት።

ይህ ገጸ በረከት ዛሬ ሲሰናዳ

እንዲቀርብ ሆኗል በመጽሐፍ ሰሌዳ።

ለሚመረምራት ከጫፍ እሰከ ሥሯ

ልዑል ሆይ ይች ዓለም ብዙ ነው ምግባሯ።

በብዙ ዐይነት ውበት የታነጸው መልኳ

አብዝቶ ይታያል ጌጥን ያለልኳ።

ይህ ሁሉ የዓለም ጌጥ ሲያዩዋት ያማልላል፤

ውስጡም ሬት ሆኖ ውጭው ማር ይመስላል።

ዓለም ለሚወዳት እመቤቱ ነች፤

ንቆ ለሚያስተውላት ትዋረዳለች።

አጭሯ ሕይወቱ ዋጋ እንድታገኝ

ሰው ምንም አይበጀው ጨዋታን ቢመኝ።

ሥጋም ወዳዊ ነው ገንዘብም ይረግፋል፤

ሀብትና ጌትነት ያለም ክብር ይጠፋል፤

ባለም ያለ ነገር ሁሉም አብሮ ያልፋል።

መልካም ስም መመሥረት ደግ መሥራት ብቻ

ለዋጋው ሰፊነት የለውም ዳርቻ።

ትክክለኛን ፍርድ የሌለውን መድሎ

እንደነ ሰሎሞን መስጠት አደላድሎ።

መሥራትና መድከም መጣጣር ከልብ

ሰው ደስ ለማሰኘት ማሰብ በጥበብ

ተጣጥሮ መግዛት ፍቅርንም ከሕዝብ

ምንም ብዙ ቢሆን የደስታ ዐይነቱ

የሚበልጠው ይህ ነው፤ የተረፈው ከንቱ!

ካባት ካያትዎ የመጣውን ቅርስ

ልዑልነትዎ ጥበብን ይውረስ።

አብቦ እሚታየው ከታደለው፥ ዘር

መልካሙ ስምዎ ታድሶ ይኑር።

# መቅድም።

ገና በልጅነቴ በትምህርት ቤት ሳለሁ መጽሐፍ ልጽፍ፥ በብዙ እመኝ ነበረ። ከዚህ ምኞቴ የተንሣ፥ ባነበኳቸው የውጭ አገር መጻሕፍት ውስጥ አልፎ አልፎ ደስ የሚያሰኝ ፍሬ ያለው ቃልና አሳብ ባገኘሁ ጊዜ በየብጣሹ ወረቀት ላይ ስጽፍ ከዚህም መካከል የሚበልጠው፥ እየጠፋብኝ የተረፈውን ባማርኛ እየገለበጥኩ ካጠራቀምኩት በኋላ እያንዳንዱን ቃል በግጥም አድርጌ በእርሳስ እየጻፍኩ ለማስተካከልና፥ ግጥሙን ለማሳመር የተቻለኝን ያኽል ፳ና ፺ ጊዜ እየለወጥሁ ስጽፈው ከዚህ በኋላ ደግሞ እንደ ገና መልሼ በሐሳቤ ውስጥ ሳይረሱኝ የቈዩትን ቃሎች ስጽፍ፥ ሳጠፉ፥ ሳርም ሳስተካክል፥ በብዙ ጊዜ ይህንን መጽሐፍ ልጨርሰው በቃሁ። አንባቢ ግን እውነት ይህ መጽሐፍ ይህንን ያኽል የሚያደክም ሆነና ነው ወይ? ሳይል አይቀርም ይሆናል። ርግጥ ነው፤ እኔም ራሴ የመጽሐፉን ጥቅም ትንሽነት ከዳካሜ ብዛት ጋራ ከማመዛዘኔ የተነሣ መጽሐፍ ልጽፍ ያለኝን ምኞት ከሐሳቤ ውስጥ ለማስወገድ ብዙ ጊዜ እስከ ማሰብ ደርሻለሁ። ነገር ግን ጨርሼም እንዳልተወው በሕይወቴ ውስጥ ከሥራ ሰዓት የተረፈኝን ጊዜ በማይረባ ጨዋታና በመቦዘን ከማሳለፍ ይልቅ ለመጽሐፍ የሚሆን አንዳንድ ነገር እየጻፍኩ የሚጠቅም ቢሆን ይቀመጣል፤ ባይሆን ደግሞ ይቀራል፤ በከንቱ ጊዜ ከማሳለፍ የማይችሉትን ሥራ መሞከር ይሻላል የሚል ሐሳብ እያነሣሣኝ ጥቂት በጥቂት ስጽፍ ብዙ መሆኑ አይቀርምና አንድ መጽሐፍ ሊመላ ትምሽ ሲቀረው ባየሁ ጊዜ ሐሳቤ እየተበረታታ ተጣጥሬ ሞላሁት።

ይህንን መጽሐፍ የጻፍኩት ትምህርት ያላቸው ኢትዮጵያውያንና ወደ ፊት የሚማሩትም ከኛ ካሁኖቹ የበለተ ከፍ ያለ ትምህርት ለማግኘት የሚችሉት ተከታዮችን የሆኑት ወጣቶች ከትምህርት ቤት ሳሉ መመኘት ትምህርታቸውን ከጨረሱ በኋላም መጣጣር የሚገባቸው መጽሐፍ እየጻፉ በራሳቸው ውስጥ ያለውንና ከየመጽሐፍቱ የሚያገኙትንም ዕውቀት ገልጠው ለሀገራቸው ሰው እንዲያካፍሉት መሆኑን ለማሳሰብና ይህንንም መልካም ሐሳብ በልባቸው ውስጥ በጣም የተነሣሣ ለማድረግ ብዬ ነው።

አለዚያማ የተማረና ያልተማረውስ ሰው በምን ይለያሉ? የተማረውም ያልተማረውም፥ ሁለቱም እኩል ይሞታሉ። ስለዚህ የተማረው ቁሚ፥ ሆኖ የሚኖር አንድ መታሰቢያ ለመተው መጣጣር ይገባዋል። ትምህርት ትቅሙ እየተስፋፋ ሲሄድ፥ ነው እንጂ ዕውቀት ያላቸው ሰዎች በጽሕፈት እየገለጡ ላልተማረው ካላሰሙት ትምህርታቸው ካንድ ቦታ ላይ ብቻ ታግዶ፥ የቆመውን ውሃ ይመስላል። ውሃ ጥቅሙ እየፈሰሰ ወርዶ ውሃ አጥቶ የደረቀውን መሬት ሲያርሰው አይደለምን? ካንድ ቦታ ረግቶ ከቆመማ ውሃነቱ ለምን ይጠቅማል።

በላይኛው መሥመር እንደ ተናገርኩት መቼም አልችልም ብሎ ከመተው የማይችሉትን ነገር ለመሥራት መጣጣር ይገባል። ሰው ልጅ ሆኖ ሳለ ቆሞ ለመሄድ አይችልም ነበር። ግን መዠመሪያ ባራት እግሩ እየዳኸ ኋላም ሲወድቅ ሲነሣ እየተንገደገደ ሲራመድ በቀን ብዛት እየለመደ ትክክል ሊራመድና ሊሄድ ሊሮጥም ይችላል። መሞከሩንና መጣጣሩና ትቶ ዝም ብሎ ቢቀመጥ ኖሮ ግን ሽባ ሆኖ በቀረ ነበር። ሁሉም ነገር እንደዚህ ነው። ማንኛውም ነገር ቢሆን ሳይዠመር ከፍጻሜ ለመድረስ አይችልም። ለመዠመር ደግሞ ማሰብና መጣጣር ያስፈልጋል። ስለዚህ ኢትዮጵያውያን የሆኑት ወንድሞቼ ከዚህ በላይ የተናገርኩትን ሁለት ፍሬ ነገሮች ሳይረሱ መዠመሪያ ስሕተት መስሎ የሚታያቸውን ነገር እያመዛዘኑ በማሳለፍ ሁለተኛ ትምህርት ያላቸው ኢትዮጵያውያን ባማርኛ ቋንቋ ተጽፈው የሚገኙት መጻሕፍት በጣም ጥቂቶች መሆናቸውን በመመልከት ከትምህርት ያገኙትን ዕውቀት እንዲጽፉ እያሳሰብኩ ከብዙ ዓመት ድካሜ የተገኘ ፍሬ የሆነውን ይህን መጽሐፍ በትሕትና አቀርብላቸዋለሁ።

# አንድ አምላክ።

እኔ ነኝ አንድ አምላክ ብሷል እግዚአብሔር
ሁሉን በጥበቤ የማስተዳደር።
የኀይለኞች ቀጪ የደካሞች ጕልበት
የምእምናን ተስፋ የፍጥረት አብነት፤
እኔ ነኝ አንድ አምላክ ጥበቤ የበዛ፤
በፍጹም ሥልጣኔ ሁሉን የምገዛ።
ለሰማይ ለመሬት እኔ ነኝ ንጉሥ
ዓለምን ፈጥሬ መልሼ እማፈርስ
ከፋትና ተንኰል ዐመፅና ሸር
አይችልም ምን ቢሆን ከኔ ሊሰወር።
ሰው ሲሞት ለይቼ ሥጋውን ከነፍሱ
የገደለም ሸሽቶ እንዳይጠፋ ዋሱ
እኔ ነኝ ሁል ጊዜ ጠበቃና ዳኛ
ደምን ለመቀበል የነቃሁ ቍራኛ
ፍርዴ በሚዛኑ ሳያወላውል
ለሁሉ እንደ ሥራው የሚያከፋፍል
የሌለ ያላየ የዘነጋ መስሎ ፍርዴ መቅሠፍት ነው ሲሰለቸው ችሎ።
የረቀቀው ዐመፅ ተረስቶ እንዳይቀር
እኔ ነኝ መዝገቡ የምቈጣጠር፤
ጌትነት ድኽነት ጤንነት በሽታ
ተድላና መጕላላት መከራ ደስታ
ሰው ቢያጣ ቢጨነቅ ቢቸገር ቢያገኝ
ሰበብ ምክንያቱ ለሁሉ እኔ ነኝ።
ከአዳም ዠምሮ እስከ ዓለም ፍጻሜ
ደግና ከፉውን ጽፌ አጠራቅሜ
ስፈርድም መልሼ ደግሞ እንደማያውቅ
ምን ሠርተኻል ብዬ ኋላ እምጠይቅ።

መልካሙን ሽልሜ ክፉን የምቀጣ
ሳልታይ አይቼ ሳልሄድ የምመጣ
በሰፊው ምሕረቴ በሌለው ወሰን
ሁል ጊዜ አድናለሁ የለመነኝን።
መንግሥቴን ዘርግቼ ባለም በሰማይ
ጽድና ኵነኔን በፍርድ የምለይ
ሳልዝምር ሳልጨርስ በክብሬ እምረጋ
እኔ ነኝ ለዘለዓለም አልፋና ዖሜጋ!

# የሰው ሐሳብ።

አንድ ቀን ሐሳቤን ተከትዬ ስሄድ
ብዙ ጓደኞች አገኘሁ እመንገድ።
ሩቅ አገር ያሉት አስቀድመው መጡ፤
ቀጥሎም የሞቱት ከጠፉትበት ወጡ።
ትክክል ተያይተን ተገናኝተን ደኅና
ሁሉም አጠገቤ ተሰበሰቡና
ጥቂት ሳይለወጥ ወዝና መልካቸው
ሳይከሱ ሳይጠቍሩ ጥንት እንደማያቸው
ሰላምታ ሰጥተውኝ ሁሉም አንድነት
የተነተጋገርን ስንጨዋወት
በፍጹም አባክኖ ሐሳቤ አታሎኝ
እውነት ይኸ ሁሉ የሆነ መስሎኝ
ልቤ ተሸብሮ እየሣቀ ጥርሴ
በጣም ደስ ብሏት ስትጫወት ነፍሴ
ፈዞ የነበረው መንፈሴ ሲነቃ
ትክ ብሎ እያየ ቢመለከታቸው
ተርገበገበና መላ ቁመናቸው
እየተጣደፉ ባፈጣጠናቸው

ተፈትም ተኋላ ተቀኝም ተግራ
እየጠፉ ሄዱ በተራ በተራ።
በዚህ የተነሣ ደንቆኝ እጅግ አርጎ
ጭራሹን ለማየት ይላል ቪክቶር ሂጎ
ሐዘን የወረረው ገብቶኝ ብስጭት
ተጕሳቁለና ልቤ በጸጸት
ተነሣ መንፈሴ ገብቶ ሊመረምር
ከቶ ምን እንደሆነ የሰው ሐሳብ ምስጢር
አይቶና ተረድቶ ሊነግረኝ ውስጡን
አሸዋ ወይ ድንጋይ ጭቃም እንደሆን
በውስጡ ያለውን አገር ለማወቅ
ካሳብ ባሕር ገብቶ መንፈሴ ቢጠልቅ
እጅግ የሚያስቸግር፥ አገኘሁ ሁከት
በዚያም በዚህ፥ በየሄደበት
የሚያገኘው ሁሉ ባይን የማያዩት
ስም የሌለው ነገር በእጅግ የማይነኩት፤
በጣም የረቀቀ ባለ ብዙ መልክ
ዐይነቱ ተነግሮ የማይተረክ
መንገዱን ሰውሮ የሚያንከራትት
ትርጓሜ የሌለው ነገር ሆነበት።
አንዱን መንገድ ትቶ ለመፈለግ ሌላ
ወደ ውስት ዘልቆ ሲሄድ እያሰላ
በጣም ጠልቆ ኖሮ ጮኸና በኋላ
የሆነውን፥ እንጃ ሲያቃስት ደንግጦ
ሮጠ መጣና ፈርቶ ተንቀጥቅጦ
አይለምደኝም አለኝ ከፉኛ ተናውጦ።
እሱስ ለካ ዘልቆ የሐሳብን ሥራ
ፈልጎ ለማግኘት ጓጉቶ ሲንጠራራ

ተገናኝቶ ኖሯል ከማያልቀው ጋራ።

## ዓለምና ጊዜ።

እኔማ አቶ ጊዜ ከጥንት ዠምሬ
ለፍጥረት ታዛቢ ሆኜ በመኖሬ
እጅግ በረዘመው በራቀው መንገዴ
ቸኵዬ በፍጥነት ሳልፍ እንደ ልማዴ
መቼም አይቀርና አይቶ መመልከት
ትልቅ ግቢ አይቼ ባለ ብዙ ቤት
ከደጅ ሲተራመስ ሰዉ፥ ከቤት ተርፎ
ይመስል ነበረ ንብ ያለበት ቀፎ።
ያጥሮቹ አሠራር የግቢውም መድመቅ
የቤቶቹም ብዛት በጣም የሚደነቅ
እንደዚህ ግቢውን ሥርቶ ያሳመረ
ማን ይሆን? አልኩና ከዚህ የሰፈረ
ደንቆኝ ስመለከት በጣም ተገርሜ
ሰው አገኘሁና አልኩት በል ወንድሜ
የዚህ የውብ ግቢ ባለቤቱ ማነው?
ያባት ያያቱ ርስት ያንድ ከበርቴ ነው
ርስቱም ዘላለም አለ ሳይነካ
ብሎ መለሰልኝ ኰርቶ እየተመካ።
    ብዙ ትውልድ አልፎ ለትውልድ ደርሼ
ደግሞ በዚያው መንገድ መጣሁ ተመልሼ።
ከዚያ ካጥር ግቢ ከዚያ ሁሉ ቤት
ከቁመቱ ርዝመት ከጐኑ ስፋት
አንድ ድንጋይ እንኳን ጠፍቶ ምልክት
ያ ያየሁት ሁሉ እንዳልነበር ሆኖ
ከግቢው ቦታ አየሁ ትልቅ መስኖ።

የለመለመበት አንድ ትልቅ ጨፌ
ተመለከትኩና ልሄድ ስል አልፌ
አንድ ትልቅ ዛፍ ሥር ተጠግቶ ጥላ
አንድ እረኛ አገኘሁ ከብቶች ሣር ሲያበላ።
እንደዚህ ያለ ሣር የበቀለበት
ከመቼ ወዲህ ነው? ብዬ ጠየቅሁት።
እሱም ቍጭ እንዳለ ቀና ብሎ አይቶኝ
ዘለዓለም ለከብቶች ግጦሽ የሚገኝ
ከዚህ መስኖ ነው ሲል መለሰልኝ።
ብዙ ትውልድ አልፎ ለትውልድ ደርሼ
ደግሞ በዚያው መንገድ መጣሁ፥ ተመልሼ።
መስኖውም ጠፋና ጨፌነቱ ቀርቶ
ከመስኩ ቦታ ላይ ከተማ ተሠርቶ
የቤቱ መበርከት የመንገዱ ማማር
የከተማው ጥዳት የግንቡም አሠራር
የሕዝቡ አበዛዝ የገበያው መድመቅ
ታይቶ እማይጠገብ እጅግ የሚደነቅ፤
ያማረች ከተማ የጥበብ መዝገብ
ጠንተው የቆሙባት ዐዋጅና ደንብ፤
ውበቷን አድንቄ ስመለከታት
ዕድሜው የጠና ሰው አግኝቼ ድንገት
መች ነው የተሠራች? ብዬ ጠየቅሁት።
እሱም መለሰልኝ በጣቱ አመልክቶ
ይች ትልቅ ከተማ ከጥንት አንሥቶ
መልኳ እየታደሰ ውበቷ እያበራ
ይኖራል ዘላለም ሥልጣኗ እንደ ኰራ።
ብዙ ትውልድ አልፎ ልትውልድ ደርሼ
ደግሞ በዚያ መንገድ መጣሁ ተመልሼ።

ከዚያች ከከተማ ጠፍቶ ምልክት
አየሁ፥ ከዚያ ቦታ ጫካ በቅሎበት።
ሲተራመሱበት ዥብ ነብር አንበሳ
በያይነቱ አውሬ፥ አዕዋፍ እንስሳ፤
ሁሉም በየቋንቋው ድምፁን እያሰማ
ለጫካው ሲሰጡት የሚያስፈራ ግርማ
የዛፉ አበዛዝ ያውሬው መበርከት
እጅግ አስደናቂ ሆኖ አገኘሁት።
ደኑን ተመልክቼ እያየሁ ስሄድ
አገኘሁ ያገር ሰው ድንገት በመንገድ።
ዛፍ ዕንጨቱ በቅሎ ጫካው የደመቀው
ከመቼ ወዲህ ነው? ብዬ ብጠይቀው
ትክ ብሎ እያየ ጫካ ጫካውን
እንዲህ መለሰልኝ እሱም ተራውን፤
ይህን መጠየቅኽ እንግዳ ነሽ ለካ፤
ጥድ የሚበቅልበት ግራርና ወርካ
ጥንቱንም ደን ነው የዘላለም ጫካ።
አንዱ ሥፍራ ሲለቅ አንዱ እየተተካ
ሁሉም ርስቴ ነች እያለ ሲመካ
ሞኝነት አድሮብን ሳናስበው እኛ
ዓለም ሰፈር ሆና ሕዝቡ መንገደኛ
ትውልድ ፈሳሽ ውሃ መሬቷም ዥረት
መሆኑን ዘንግቶ ይህ ሁሉ ፍጥረት
ስትመለከቱት በሰልፍ ተጉዞ
ሁሉም በየተራው ያልፋል ተያይዞ።

# የሰው ዕድል።

ጎይለኛው ባላልጋ የኢትዮጵያ ንጉሥ
የመቅደላ ዳኛ ዐፄ ቴዎድሮስ
ከጥንት ዠምሮ ከድኽነታቸው
እጅግ ብዙ ጊዜ ያገለገላቸው
በጣም የሚወዱት ሎሌ ነበራቸው።
እሱም በጣም አዝኖ እየተመረረ
እንዲህ ሲል አንድ ቀን ቀርቦ ተናገረ ፡
እግዜር ያሳይዎ ግርማዊ ጃንሆይ፤
ችግሬን ላመልከት ጕዳቴን ላሳይ።
እኔ አሽከርዎ የጥንቱ የጧቱ
ይኸው ብዙ ዘመን ስለፋ በከንቱ
ስንቱ ኋላ መጥቶ ማዕርግ ሲያገኝ
ምነው እኔ ብቻ ቀን አይሞላልኝ።
እንኳንስ ለንጉሥ ላንዳንዱ ሻለቃ
ስንት ሰው ነው አድሮ ለማዕርግ የበቃ።
በታማኝነቴ እንደዚህ ጠንቼ
ግርማዊነትዎን ስኖር ተጠግቼ
እንዴት እኔ ብቻ ልቅር ተረስቼ።
ፍርድ አስተካካዩ የብይኑ ጌታ
እያዘኑ ሰምተው ይህን አቤቱታ፤
በምሥጢር ጠሩን አንድ የልፍኝ አሽከር
ባንዱ ብር ሞቶ ባንደኛው ዐፈር
በመልኩ በጕኑ የሚመሳሰል
እንዲያመጣ አዘዙት ሁለት አገልግል።
ከዚህም በኋላ ሎሌያቸውን ጠርተው
ሁለቱን አገልግል ከመሬት አድርገው
መርጠኸ ከሁለቱ እንደምትፈልገው

አንደኛውን ውሰድ ብለው አዘዙት፤
ሎሌው አስተያይቶ ባይኑ መዝኖት
መርጦ ወሰደና አንዱን አገልግል
ከውስጡ ያለውን ፈታና ቢያስትውል
ዐፈሩን ስላየ በጣም ተሣቀቀ
ጠላቱም ዕድሉ መሆኑን ዐወቀ።
ንጉሡም መልሰው እንደዚህ አሉት፤
ጥንቱን ሲፈጠሩ ፊት ካልታደሉት
ክብርን ጌትነትን ሰው ቢያስብ ቢመኘው
ሕምል ነው፤ ተረት ነው፤ መቼም አያገኘው።
ያርባ ቀን ዕድልኽ ሆኗልና ግራ
ልሥራልኽ ብል እንኳን የቸርነት ሥራ
ከተሰጠኝ ዕጣ አያልፍም ሚዛኑ፤
ስለዚህ ይቅርብኽ ከኔ ላይ ማዘኑ።

ዐፄ ቴዎድሮስ መልካም መረመሩ፤
ስለ ሰው ልጅ ዕጣ ዕውነት ተናገሩ።
ረኸሙን ሰው ማቅላት ቀዩን ጥቍር ማድረግ
ብልኆች ጠቢባን አልተቻላቸው፤
ዕድልም እንዲህ ነው መድኀኒት የለውም።
የሰው ልጅ ሞኝ ነው ዐሥሩን ይመኛል፤
ዕጣው ያልሰጠውን እንደ ምን ያገኛል?

# የሰው ጠባይ።

አንድ ቀን እግዚአብሔር አራዊቱን ሁሉ
ተሰብሰቡ ብሎ አዘዘ በቃሉ።
በእስትንፋስ ተፈጥሮ ቆሞ እሚንቀሳቀስ
ካንበሳ ዠምሮ እስከ ትንኝ ድረስ
ከሩቅ ቦታ ሳይቀር ሁሉም እየሮጡ
ቃሉን ለመፈጸም ተሰብስበው መጡ።
ሁሉም ቀረቡና አንድ እንኳ ሳይቀር
ተከማችተው ሳሉ ከዙፋኑ ሥር
አስቀድመኽ አንተ እስቲ ወደዚህ ና
ብሎ አምላክ ፊት ዝንጀሮን ጠራና
እነዚህን ሁሉ አይተህ ንገረኝ
መልካቸው ከመልክኽ በልጦብኽ ቢገኝ
ገልጠኽ የልብኽን ንገረኝ አትፍራ
አድሳለሁ አለው በጐደለው ሥፍራ።
ዝንጀሮ መለሰ አቤቱ ጌታዬ
ፊቴና ደረቴ እጄና ጭራዬ
ውብ ሆኖ ተሠርቷል ምን ጐደለ ብዬ
ምኔ አስቀየመና ምኑን ልለምን፤
እንደ ቀኡት ሁሉ እግር የለኝምን?
ይልቅ አቶ ዥብን ብታድሰው ምነው፤
አፉ በጣም ሰፊ እግሩም አንካሳ ነው።
ቀርቦ ቢጠይቁት ዥብም ተጠራና
ምን ጐደለኝ አለ መልኬ ሁሉ ደኅና፤
ይልቅ እንደ ገና ዝኆን ተመልሶ
እጅግ መልካም ነበር ቢፈጠር ታድሶ።
ይገባል እግዚአብሔር አሳቤን ቢቀበል
ከጆሮው አንሥቶ ጭራው ላይ መቀጠል።

ዝኆንም ብቅ ሲል ሁሉም እየሣቁ
አድሰኝ ይለዋል ብለው ቢጠይቁ
ዝኆን ግን መለሰ መልኬን ሁሉ ደኅና
አድርጎ ለሠራኝ ይገባል ምሥጋና።
እኔስ እስከ ዛሬ በመልኬ አፈጣጠር
አላየሁበትም የሚያስከፋ ነገር።
መታደስ የሚያሻት ዓሣ ነባሪ አለች
መልክና ቅርጽ አጥታ የተደበለበለች።
ዘለዓለም መሣቂያ ሆና ከምትቀር
እሷ እውነት ያሻታል መልሶ መፈጠር
እሷና ሌሎቹ ሁሉም ቢጠየቁ
አንዱ ባንዱ ሲያሾፍ እየተሣሣቁ
ይህ ነገር ጐደለኝ መልኬ በዚህ ከፋ
አድሰኝ ፍጠረኝ ብሎ የሚል ጠፋ።
እግዚአብሔርም አይቶ በመካከላቸው
ነውሩን የሚናገር እንደሌለባቸው
በሉ ሂዱ ብሎ አሰናበታቸው።
ይህ ባውሬ ምሳሌ የተወራው ተረት
መልካም ማስረጃ ነው ለሰዎች ከንቱነት፤
እንደነ ዝንጀሮ ሳላስቀረ ውጩ
እስቲ ነውራችንን ልናገር ገልጩ
ስንመለከተው ተመልሶ ለኛ
እጅግ ያለመጠን ያሥቃል ክፉኛ
ደግ ሰው ጨዋ ሰው የሚሉ ዐማርኛ።
ትንሽ፤ ቀላል፥ ኢምንት ደካማ፥ ወራዳ፥
ከንቱ ፍሬ ቢሶች ዐመለ ገዳዳ
ክፉ አይደለንም ወይ የሰው ልጅ ስንባል?
ይህንን በውነቱ ልናውቀው ይገባናል፤

ግን እንደበታችን በባሕሪው ተለምዶ
መናገር አይወድም ድዳነትን ወዶ።
ቀጣፊ ሰው፥ በዕውር ዕውሩ በሻባ
ሽባው በበራ በራው በተብታባ
ተብታባ በኰሩ ኲሩው በመላጣ
መላጣው በመልቲ መልቲ በገጣጣ፤
ገጣጣው በቢስ ቢስ በቀናተኛ
አንዱ ባንዱ ሲያሾፍ እርስ በሳችን እኛ
ለመሣቁ ጊዜ ደስ ደስ ይለናል
የተዘጋውም አፍ ይከፈትልናል።
ተግሣጽ የማይቀጣው ሰው የሚሉ ጉድ
ምን ጊዜም አይተወው ይህንን ልማድ።
ብዙ ትውልድ አልፎ ይምጣ አዲስ ዘመን
ሰዎች አንቀጣም ዘለዓለም ያው ነን።
እንዳይመሳሰል በመልክ ሰው ሁሉ
የተሠራበትም ልዩ ነው ዐመሉ።
መልኩና ዐመሉን አስተውለን ብናይ
አሌ የምንለው ሐቅ አይዶለም ወይ
ፍጹም ሰው ላይገኝ በዚች ዓለም ላይ።
ይኸ ሁሉ ፍጥረት ምድርን ያለበሰው
ደግሞ ይባል ጨዋ ጥሩም ይሁን ሊቅ ሰው
በጠቅላላው ሆኖ አንደኛው ሳይቀር
ሰው ሁሉ ጐድሎ ተደርጎ ሲፈጠር
አንዱ ባንዱ መሣቅ መች ይገባ ነበር።

# የግፈኞች ፍርድ።

ባራዊት መካከል በሽታ ተነሥቶ
ሁሉም ተጨነቁ ሕመምተኛው በዝቶ፤
ሳይበሉ ሳይጠጡ ብዙ ቀን ሆናቸው፤
ሲወድቁ ሲነሡ ሕመም ተጭኗቸው።
ከሁሉም ኀይለኛው አንበሳ እንዲህ ሲል
ጮኾ ተናገረ ቆመና መካከል፤
ታሪኩ እንደሚለን ጥንትም የግዜር ቍጣ
ተልኮ ለቅጣት ባለም ላይ ሲመጣ
ዕጣ በመጣጣል ወይም በኑዛዜ
ዐመፅ የሠራ ሰው በተገኘ ጊዜ
ፍርዱን ተቀብሎ ባመፁ ሲቀጣ
ካለም ላይ ይጠፋል የወረደው ቍጣ።
ስለዚህ አሁንም በኛ ላይ መቅሠፍቱ
በኀጢአት ነው እንጂ አልመጣም በከንቱ፤
ከመካከላችን ክፉ ዐመፅ የሠራ
አይጠፋም እንፈልግ እናድግር ምርመራ።
ክፉ ሥራችንን አንድ እንኳ ሳይቀር
ከራሴ ዠምሬ ሁሉን ልናገር።
ሁል ጊዜ ሲርበኝ የምበላው ሳጣ
በጉን ከነረኛው ጠብቄ ሲመጣ
ሥጋውን በልቼ ደሙን የምጠጣ
እንዲያ ሲጨነቁ የጨከንኩባቸው
አይቀርም ይደርሳል ከግዜር ፊት ደማቸው።
ይኸ ሁሉ ግፍ ነው መቅሠፍት የሚያመጣ፤
ምንም ቅር አይለኝ በፍርድ ብቀጣ።
እናንተም እንደ እኔ ሳትዋሹ ሳትፈሩ
ያጠፋችሁትን እስቲ ተናገሩ።

ቀበሮ መለሰች እንደዚህ ስትል
እርስዎ የሠሩትን ተመልካች ሲያስተውል
በጉን ከነረኛው ተርበው ቢበሉ
ኀጢአቱስ የት አለ ምንድነው በደሉ?
ይልቅስ ተርበው እርስዎ ሲበሏቸው
ለበጉም ለረኛው ትልቅ ነው ክብራቸው።
ዝኆንና ነብር ዥብና አውራሪሥ
ቀጥለው በተራ ያጠፉትን ነፍስ
ያፈሰሱትን ደም አንድም ሳይደብቁ
ይህንን ሠርተናል ብለው አስታወቁ።
ግን ካደባባዩ የነበሩት ሁሉ
ፈርተው በሚገባ መፍረድ ስላልቻሉ
ጥፋታችሁ በጣም ቀላል ነው እያሉ
ምንም ሳይወቅሷቸው እንኳንስ ሊቀጡ
ቀላል ነው አሏቸው ሁሉም ነጻ ወጡ።
አህያ ብቅ አለች ከሁሉም በኋላ
ትናዘዝ ጀመረ እሷም እንዲህ ብላ፤
አንድ ቀን ተጭኜ ደክሞኝ ስንገላታ
ጌታዬ ሲነዳኝ በዱላ እየመታ
ግጦሽ ሣር አይቼ የሚያምር፥ በመስኩ
አንድ ጉርሻ በላሁ ሌላም አልደገምኩ
ርግጥ ነው ዐውቃለሁ መሆኑን የሌላ፤
ግን ሰይጣን ገፋፋኝ ሰርቄ እንድበላ።
ይህንን ሲሰሙ ሁሉም አንድነት
የስድብ የርግማን የቍጣ መዓት
እያከታተሉ አወረዱባት።
ቀበሮም ተነሥታ ያላንዳች ምሕረት
አንች አመዳም ርጉም እከካም ፍጥረት

ለካ ባንቺ ጦስ ነው ይህንን በሽታ
በሁላችንም ላይ ያመጣብን ጌታ።
እንዴት ትደፍሪያለሽ የሰው ሣር ለመብላት
ሞት ነው ሌላም አይደል የሚገባሽ ቅጣት
ብላ ከሁሉ ስም ጨረሰች ተናግራ፤
ፍርዱም በዚህቆመ አለቀ ምርመራ።
እዚያ የነበሩት የምድር አራዊት
አዎን አዎን ብለው ይገባታል ሞት
ምስኪኗን አህያ ተከፋፈሏት።
እውን የሷ ዐመፅ ነው የፈጣሪ ቍጣ
ባራዊት ሁሉ ላይ ጐትቶ ያመጣ?
ከተናዘዙትስ ካራዊቶች ውስጥ
የሷ አመፅ ኗሯል ወይ በእውነት የሚበልጥ?
ያም ሆነያም ሆነ አልዳነችም እሷ
ትቀጫለች አሏት በሥጋ በነፍሷ።
እንሆ ባለም ላይ በዳኝነት ሥራ
ጉባኤ ተደርጎ ሲጨረስ ምርመራ
ፍጻሜው እንዲህ ነው ስናየው በውነቱ
መሥዋዕት እየሆነ ደካማ ለብርቱ
ያልታደለው ድኻ ይጠፋል በከንቱ።

# አባት ልጅ አህያ።

አንድ የባላገር ሰው ገንዘብ ቸግሮት
አህያውን ሊሸጥ ተነሥቶ በጧት
አህያውም ሲሄድ እገበያ ድረስ
ደክሞት እግሩን አስሮ በደኅና ቀላድ
ወንድ ልጁን ጠርቶ አለው እንሂድ፡
ልጅና አባት ሆነው አህያን ሁለቱ
ተሸከመው ሄዱ እየተጫወቱ።
ገና መዠመሪያ አንድ ሰው ሲያያቸው
ስለ ተገረመ በዚህ በሥራቸው
ደንቆት እንደዚህ ሲል ጮኾ ተናገረ፤
ሳይሠራ እስካሁን ባለም ላይ የቀረ
ከሌላው ጉድ ሁሉ ይህ ብቻ ነበረ፤
ዛሬስ ብሎ ብሎ ሥራ ቢያጣ ደግሞ
አህያ በጫንቃው ሰዉ ተሸክሞ
ይንቀረፈፍ ዠመር ይኸው ባገራችን
እንዲህ ያለ ታሪክ አልሰማም ጆራችን
ይልቅስ ሌላ ሰው አይይ ይህን ጉድ
አህያውም ይውረድ በእግሩ ይራመድ
ብሎ ስላሾፈ በሣቅ በዘለፋ
ስለ መሰላቸው በውነት የሚያስከፋ
አባትና ልጁ አህያውን ፈተው
ይነዱት ዠመረ እንደ ደንቡ ገብተው።
ከትከሻ አውርደው እንንዳኸ ቢሉት
ከዕረፍት ወደ ድካም ስለ ሆነበት
አህያው ለግሞ መቆም ስላመጣ
ልጅየው ተናዶ ካህያው ላይ ወጣ።
ከዚያም እየመታው በደኅና ጐመድ

ይዳዙ ዝመረ በዋናው መንገድ።
አንድ ሽማግሌ ራሰ መላጣ
ይህን ነገር አይቶ እንዲህ ሲል ተቈጣ፤
መቼም የዛሬ ልጅ ለምንም አይረባ
አባት በእግሩ ሲሄድ ልጅየው በከብት
ምነው በልጁ ሲሄድ ልጅየው በከብት
ምነው እንዲህ ነወይ ሲከበር አባት
ብሎ በልኩ ላይ ተግሣጽ ቢናገር
መልስም አልመለሰ፤ ሳይከራከር
ደንግጦ ልጅየው ወረደና ቶሎ
አባት ተቀምጦ ልጁ ተከትሎ
ጥቂት እልፍ ብለው ቍልቍለት ሲወርዱ
ሦስት ወይዛዝሮች አንድነት ሲሄዱ
አንዷ ተናገረች እንደዚህ ስትል
ልጁን አስከትሎ አሽከር ይመስል
ደልቶት ካህያ ላይ ይህ የተቀመጠው
ሲሆን ቢወርድለት ወይም ቢያፈናጥጠው
ቢለወጥ ነው እንጂ ጊዜና ዘመኑ
አባት በልጁ ላይ እንዲህ መጨከኑ።
አባትዮው ሰምቶ ይህንን ስትል
ነውር መስሎ ታየው ልጁን ማስከተል፤
ደስ የበላት ብሎ ጠርቶ አፈናጠጠው።
አባትና ልጁ አንድነት ተቀምጠው
ጥቂት እንደ ሄዱ አንድ ሰው አይቷቸው
ተራውን ሣቀና እንደዚህ አላቸው፤
አሁን ይህ አህያ እገበያ ድረስ
እውነት ይችላል ወይም ሳይሞት ለመድረስ?
እንደዚህ ሆናችሁ ገበያ የምትወጡ

ምናልባት ይሆናል ቈዳውን ልትሸጡ
አሁንም ይሻላል ብትወርዱለት
አህያችሁ ደክሞ መንገድ እንዳይሞት።
ሰምተው እንዳልሰማ አልፈው እንዳይሄዱ
አባትና ልጁ ሁለቱም ወረዱ።
አህያው ሌጣውን እነሱም በግራቸው
ይጓዙ ዠመረ ወደ ገበያቸው።
ይህ አልበቃ ብሎ ጥቂት እልፍ ሲሉ
ሰዎች ሣቁባቸው እንደዚህ እያሉ፤
ሌጣ አህያ ነድተው ፊት እያስቀደሙ
የማናቸው ጅሎች በእግር የሚደክሙ?
ሌጣ አህያ ነድቶ በእግር መኳተን
ትልቅ ከብትነት ነው አህያ መሆን።
አባት ይህን ጊዜ መለሰ እንዲህ ሲል፤
በጣሙን ሲያንሰኝ ነው አህያ መባል
ባለማወቃችን በጣም ተታለን
ሁሉን ደስ ማሰኘት የሚቻል መስሎን
ሰው በሣቀ ቍጥር እውነት መስሎን ጉድ
ይህን ሁሉ ጉዞ ይህንን መንገድ
ዘለቅነው እስከዚህ ስንወጣ ስንወርድ።
ከእንግዲህ ወዲያ ግን ይጥላም ይቀበል
በቃኝ የሰው ነገር ሰምቶ መከተል።
  እንሆ እንደዚህ ነው የዚህ ዓለም ጣጣ፤
  ማንኛውም ነገር ተቃንቶ ቢዋጣ
ሰዉ በሰው ነገር የሚለው ላያጣ
የሁሉን ቃል ሰምቶ እንዴት ይዘለቃል፤
    ሰው ለራሱ ጥቅም ያሰበው ይበቃል።

# ደግነትና ክፋት።

አንድ ሰው ነበረ ቅንነትን ወዳድ
ለሁሉ ማዘንን አድርጎ እንደ ልማድ
ይኖር የነበረ ነቅቶ እንደ ዘበኛ
ደግ ሥራ ለመሥራት ልቡናው ሳይተኛ።
አንድ ቀን ማለዳ ተነሥቶ ሲሄድ
እባብ ወድቆ አገኘ ከማኸል መንገድ
አመዳይ ጥሎበት ውርጭ አቄራምዶት
ዐሥራ አምስት ደቂቃ የቀረው ሊሞት
ሰውየውም አዝኖ ይህን በማየት
ከመሬት አንሥቶ በጁ ጨብጦት
ከቤቱ አገባና በድኑን እባብ
ዘርግቶ አስቀመጠው ምዳጃ አጠገብ።
እሳት እያሞቀ ጥቂት እንዳቄየው
ዕጥፍ ዘርጋ እያለ ሲነቀሳቀስ አየው።
ኹለተኛው ሞቆ ሕይወት ሲሰማው
ተንኰልና ቊጣ አንድነት ሆነው
የተፈጥሮው ክፋት በልቦናው መጥቶ
የሚነክሰው ሲሻ ምላሱን አውጥቶ
ሞቶ ነበረ ያ በድን ሬሳ
ያዳነውን ሊነድፍ ራሱን አነሣ
ሰውየውም አይቶ ይህን አኳኋን
በሥራው ደግነት አዘነ በውን፤
ምንም ክፋት ለሱ ገንዘቡ ባይሆን
ደጉን ክፉ አድራጊ የተገባ ቊጣ
እንደ እሳት ተፋጅቶ በልቡ ላይ መጣ፤
መጥረቢያ አነሣና እባቡን ቢለው
ካራት ላይ ቈርጦ በጣጥሶ ጣለው።

ሰው ደግ ሲውልለት እባብ እየከዳ
በደግ አድራጊው ላይ መርዙን አሰናዳ።
ክፉም ሰው እንደዚህ የክፋቱ ክፋት
ደግ የዋለለትን ያስባል ለማጥፋት፤
ተንኰሉም ባሰበው መንገድ መሄድ ትቶ
የገዛ ጥፋቱን ያመጣል ጐትቶ።

# ምሥጢርና ወሬ።

ምሥጢር አጫውተዋት ምን ቢሏት አደራ
ጠብቃ የምትኖር ለሰው ሳታወራ
ባለም ላይ ምንም ሴት አትገኝም ከቶ
ብለው በጨዋታ ሲናገሩ ሰምቶ
አስቦ ሊረዳ እውነትነቱን
አንዱ ሰው ፈለገ ሚስቱን ሊፈትን።
ማታ መብራት ጠፍቶ ሁለቱም ተኝተው
ምነው ሆዴን ወጋኝ አንገሯቴን ጐተተው
የነካኝን አንጃ እባክሽ ተነሺ
እስቲ መብራት አብሪ ልብስሽን ልበሺ
አለና ሚስቲቱን ባልዮው አስነሣት፤
እሷም ቶሎ ለብሳ አነደደች እሳት።
አንቺ ልጅ ጉድ ባይ ጉድ መጣ በኔ ላይ
ዕንቍላል ወለድኩኝ፤ ልክ የዶሮ መሳይ
አለና እውነትም የዶሮ እሚመስል
ሰጣት ለሚስቲቱ ትኩስ ዕንቍላል፤
እሷም በጣም ገርሟት እያገላበጠች
ካየችው በኋላ ወስዳ አስቀመጠች።
ባልዮው ለሚስቱ እንደዚህ አላት
ይህ ነገር እንግዴህ እንዲያው ምናልባት

ሰው ቢሰማውና አገር ቢያወራው።
ለኔም ሆነ ላንቺ ትልቅ ነውር ነው
ለሰሚው መሣቂያ መሆኔን ዕወቂ
ለማንም አታውሪ በጣም ተጠንቀቂ።
ሚስቲቱ መለሰች ወሬ እንዳይወራ
አለ ብዙ ጊዜ የሚባል አደራ
ይኸ ለራሱ ጉድ ታይቶ ያልታወቀ
እንዲያው ይቅር እንጂ እንደ ተደበቀ።
ይህን ተባብለው ሁለቱም ተስማምተው
ከተኙ በኋላ መብራቱን አጥፍተው
ሴቲቱ ነገሩን በትመለከተው
ብታሰላስለው አውጥታ አውርዳ
ጥቂት ቀረው ልቧ ገርሞት ሊፈነዳ።
በጣም የሚያስደንቅ ሆነና አገኘችው፤
እንዳትጠራጠር ባይኗ ነው ያየቸው።
እንዴት ወጣ ዕንቍላል ከወንዱ ሆድ ውስጥ
ይኸ ነገር ገርሟት ስትቅበጠበጥ
እንቅልፍ ባይኗ ሳይዞር ስትገላበጥ
እንዳይነጋ የለም ነጋና ማለዳ
ውሃም የለኝ ብላ ተነሣች ልትቀዳ፤
በንሥራ ያለውን አፍሳ ከውጭ
ጎረቤቷን ጠርታ ሄደች ወደ ምንጭ።
ሁለቱም ሲሄዱ መንገድ ለመንገድ
ስሚ እቴ ልንገርሽ አንድ ትልቅ ጉድ፤
ትናንትና ማታ ታሞ የኔ ባል
አምጦ ወለደ ሁለት ዕንቍላል
እንዲህ ያለውን ጉድ ለማንም መናገር
ምንም ቢሆን ከቶ አይገባም ነበር፤

ነገር ግን በኔ ዘንድ ምሥጢር እውነት ኖሮ
ለማ ልንገረው ነው አላቺ ተሰውሮ?
ያገር ሕዝብ ይህን ጉድ ሰምቶ እንዳያወራ
ለማንም ሰው ቢሆን አትንገሪ አደራ
ብላ እየመለሰች አስጠንቅቃ ነግራ
ምላ ተገዝታ ያቺም ላታወራ
ምሥጢሩን ተካፍለው ተለያይተው ሄዱ።
ያቺም በተራዋ እጅግ ደንቋት ጉዱ
በሆዷ ልትይዘው ልትይዘው አልቻለችምና
እንዷ ወዳጅዋ ዘንድ ሄደችና ፈጥና
ትናንትና ማታ የወዳጄ ባል
ወለደ አለቻት አሥር ዕንቍላል።
ያቺም በበኩሏ ላንዷ ነግራ ቶሎ
ኻያና ሠላሳ ስማኒያ ተብሎ
አንዷ ላንዷ ነግራ በመጨማመር
በለመገኘቱ የሚመራመር
ቍጥሩም ከወሬው ጋር እየበዛ ሄደ
አቶ እገሌ መቶ ዕንቍላል ወለደ
ተብሎ ማታውን ወሬው በመንደር
ተነዛ ይባላል ባንድ ቀን ጀንበር።

> አትበቃም ሲባል ለምሥጢር አደራ
> ምንም ይኸ ተረት በሴት ስም ቢወራ
> ለመቅለል እንደሆን ምሥጢር ለማውራት
> የወንዶች ምላስ ይብሳል ከሴቱ ፡
> ልብ ስልቻ ነው ምሥጢር የሞሉበት
> ማሰሪያው ምላስ ነው የተቋጠረበት፤
> ጠብቀው ካልያዙት የዘነጉ ለታ
> ይፈሳል ምሥጢሩ ማሰሪያው ሲፈታ።

# በዐመፃ የመጣ ገንዘብ።

አንድ ሀብታም ነጋዴ ሲጓዝ አግኝተው
ሦስት ሌቦች ሆነው ወርቁን ቀምተው
እሱንም አርደውት ከጒድባ ጣሉት።
ሁለቱ አንደኛውን እንደዚህ አሉት፤
ለችግር ነውና ገንዘብ መገኘቱ
ምግብ ከከተማ ገዝተኸ ባየይነቱ
ሳትውል ሳታድር ይዘኸ በቶሎ ና፤
ጦም ውለን ጦም ካደርን ብዙ ቀን ነውና።
እሱም እሺ ብሎ ተነሥቶ ሲሄድ
እንዲህ ሲል አሰበ መንገድ ለመንገድ
አብረውኝ ባይኖሩ እኒህ ጓደኞቼ
ወርቁን ለኔ ብቻ ወስጄ አስቀርቼ
ወርቁን ለኔ ብቻ ወስጄ አስቀርቼ
እክብር ነበረ አሁን ግን አስቀርቼ
እክብር ነበረ አሁን ግን ለሦስት
ሲከፈል ይሆናል ድርሻችን ጥቂት።
አስቦ ብቻውን ወርቁን ለመውሰድ
ዘዴ በመፈለግ ሲያወጣ ሲያወርድ
መርዝ ፈለገና ከሚበሉት ውስጥ
ጨምሮ ወሰደ ለነዚያ ሊሰጥ።
እነዚያም ባንድ ወገን እንደዚህ አሰቡ
ወርቁስ ብንሸጠው ብዙ ነው ሒሳቡ
ብቻ ምን ይሆናል ያ የኛ ጓደኛ
ተካፍይ የሆነ አለብን ሦስተኛ
ግን ለሁለታችን ብቻ ብናስቀረው
የሚያንሰን አይደለም ድርሻን በቂ ነው።
ተማክረው ሲመጣ በጩቤ አርደውት

ሬሣውን ከጉድባ ወዲያው ጨመሩት።
ተርበዋልና ቶሎ እንደ ቸኰሉ
ምግቡን አሰናድተው ምሳቸውን በሉ።
ጥቂት እንደ ቈዩ ሕመም ተሰማቸው፤
መርዙ ተሠራጭቶ በሰውነታቸው
ወዲያው ሁለቱንም እዚያው ገደላቸው።
ከነከረጢቱ ወርቁ እንደ ታሰረ
ባለቤት የሌለው ገንዘብ ሆኖ ቀረ።
　　በመሥራት ነው እንጂ ላብን በመጥረግ
በመስረቅ በመንጠቅ የለም መበልጠግ።
ቀኁጥራቸው ብዙ ነግ ግፍ ሠርተው በከንቱ
ባመፅ የሰው ገንዘብ ሰብስበው ሲከቱ
ደም እያነቃቸ ሳይበሉት የሞቱ።

# የሀብት ትዕቢት።

ብዙ ብርና እኸል በጭነት የያዙ
ሁለት አጋሰሶች አንድነት ሲጓዙ
ብሩን የተጫነው ጓደኛአውን አለው
እንዴት አንተን ከኔ እኩል አስተካክለው
አብረን እየነዱን እኩል እንሂድ
እኔ ተከብሬ በጣም ብወደድ
አደራ ሰጥተውኝ ብር ጭነውኛል፤
ካንተ ግን ያነሰ ምን ፍጡር ይገኛል።
እነሱም ዐውቀውት መሆንህን ታናሽ
አድርገውኽ ቀሩ እኽል አመላላሽ
መራመድኽ ቀርቶ እኩል ከኔ ጋራ
መሥራት ይገባኻል የሥልጣኔ ሥራ
ይልቅ የልተቀጣ ባለጌ አትምሰል፤

ወደ ኋላ ቀርተኸ እኔን ተከተል
እያለ በንቀት ሲናገር ትዕቢት
ሁለት ሌቦች ወጥተው ካደፈጡበት
እኸሉን ተዉና ብሩን ሲፈልጉ
በዱላ ደብድበው በጩቤ እየወጉ
ብር የተጫነውን አጋሰሱን ገድለው
ወሰዱት ይባላል ብሩን ተከፋፍለው።
አስተውለኸ አንባቢ መሆኑን ትምህርት
የዚህን ምሳሌ ምሥጢር ተመልከት፤
ከብሬያለሁ ብሎ ሰውም እንዳይኰራ
በገንዘብም እንዲህ አለበት መከራ።

## የከፋት ተጋብኦነት።

ከሰል የሚሸጥ ሰው ልብስ አጣቢን አለው
ለቤት ኪራይ ብለኸ ገንዘብ የምትከፍለው
ቀሪ እንዲሆንልኸ አብረኸ ከኔ ጋራ
ኪራይ ሳትከፍል ተቀምጠኸ ብትሠራ
ቤቱም ይበቃናል አንድነት እንኑር።
ልብስ አጣቢ ሰምቶ ይህንኑ ምክር
አመሰግናለሁ በማሰብኸ ለኔ
ግን የማይጠቅመኝ ነው ካንተ ጋር መሆኔ
ታጥቦ ታጥቦ ጭቃ የሚባለው ተረት
እንደሚደርስብኝ አስበኸ ተመልከት
እኔ የማጥበው ልብስ ካንተ ከሰል ጋራ
ይቆሸሽ የለም ወይም አብረን ስንሠራ
ከሰል ለነጭ ልብስ ነውና ጠላት
የማይሆን ሐሳብ ነው ሲል መለሰለት።
ከሰል ለነጭ ልብስ እንዲሆነው አጥፊ

ከክፉም የዋለ ክፉትን አትራፊ
ከመሆን አይድንም ምን ቢጠነቀቅ
ዐመል ሳይበላሽ ጠርቶ እንዲጠበቅ
ከመጥፎ ጓደኛ ይገባል መራቅ።

# ሁለት ወንዳማቾች።

ያንድ እናት ያንድ አባት ሁለት ልጆች
ታላቅና ታናሽ ወንድማማቾች
አባታቸው ሞቶ ቅርሱን ሲካፈሉ
ሁለቱ አንድ አህያ ደረሳቸው አሉ።
ታናሽ ድኻ ነበር ታላቁ ግን ጌታ
እንዳይቀርባቸው የሁለቱም ፈንታ
ታናሽ እንሽጥ ቢል ታላቁ እንረድ
በዚህ ተጣሉና ሄዱ ወደ ፍርድ።
የሁለቱን ሐሳብ ዳኛ ተመልክቶ
የታላቁን ተንኰል መርምሮ ተረድቶ
መሸኘት ቢያቅተው ሁለቱን አስማምቶ
ታላቁ እንነቢ ብሎ እንረደው ካለ
የሚከለክለው ምንም ነገር የለ
አለና ባጭሩ ብይኑን ሰጣቸው፤
አህያውም ታርዶ ተከፍሎ ድርሻቸው
ሀብታሙ ድርሻውን ሰጠ ለውሾቹ
ከዚያን ቀን ዠምሮ ወንድማማቾቹ
በጠብ ተለያይተው ተቀያይመው ቀሩ፤
ካባታቸው ርስት ተካፍለው ሲኖሩ
ሀብታሙ ታላላቅ አዳራሾች ሠርቶ
ታናሹም ለብቻው ካንድ ጐዦ ገብቶ
ቂም ይዞ በሆዱ ወንድሙን ሲጐዳ

ብድሩን ሊመልስ አንድ ቀን ማለዳ

ከቤቱ ተነሥቶ ዛሬ ይኸውና

ጐጆዬን ማቃጠል ፈልጊያለሁና

ካዳራሾችኽ ላይ እሳቱ እንዳይደርስ

ቶሎ ዘዴ ፈልግ ኋላ እንዳታለቅስ

አለና ነገረው ለታላቅ ወንድሙ፤

የወንድሙ ሰዎች ይህንን ሲሰሙ

ሁሉም ተሸበሩ ወንድሙም ተናዶ

ባንተ ጐጆ ሰበብ ቤቴ ለምን ነዶ

የጐጆኽን ዋጋ ሒሳቡን ሰጥቼ

አስቀራለሁ እንጂ በገንዘብ ገዝቼ

ቢለው ታናሽየው ምነው ምን ቢያቀብጥ

ዐይኔ እያየ ላንተ ቤቴን የምሸጥ።

ማን ይከለክላል ባደርግ እንዳሳቤ

አቃጥለዋለሁ በገዛ ገንዘቤ።

በዚህ ተጣሉና ወደ ዳኛ ወጥተው

ዳኛውም አየና ማስታረቅ ቢያቅተው

ወዶ ከተነሣ ቤቱን ለማቃጠል

እንዴት ይቻለናል እኛ ለመከልከል

ብሎ ለታናሹ ስለ በየነለት

እሳት ከጐጆው ላይ ወስዶ ለኰሰበት።

እሳቱንም ነፋስ እያስተላለፈው

ከዚያ ሁሉ አዳራሽ አንድ እንኳ ሳይተርፈው

ባዶ ሜዳ ቀረ ሁሉን አቃጥሎት፤

በኋላም ታናሹ ድርሻውን መሬት፤

አርሶና አለስልሶ ዐተር ዘራበት፤

የወንድሙ ልጆች ዐተሩ ሲሸት

እንቡጡን ፈልፍለው ሲበሉ ያዛቸው፤

የበሉት ዐተር አሁን አምጡ አላቸው፡፡
ወንድምየው ደርሶ እከፍላለሁ ቢለው
ለምንድነው እኔ ዋጋ እምቀበለው
አሁኑኑ ቀደው ከሆዳቸው ያውጡ
የበሉትን ዐተር ቶሎ ካላመጡ
አለቅም አለና ልጆቹን ያዛቸው፤
ወድማማቾቹ እንደ ልማዳቸው
ፍርድ ይለየን ብለው ደግሞ በዚህ ነገር
ተጣልተው ለሙግት ሄዱ ወደ ወንበር፡፡
ያመጣበት ዳኛ ነገሩን አስተውሎ
ታናሹን ተከሰኸ ተገላገል ብሎ
ታናሹ እንቢ ብሎ ኀይለ ቃል፥ ቢያመጣ
እንግዲህ ዐተሩን ከሆዳቸው ያውጣ
ምን ማድረግ ይቻላል አለና ፈረደ፤
የወንድሙን ልጆቹ ሆድ እየቀደደ
ታናሽየው ልጆቹ ሆድ እየቀደደ
ታናሽየው ወንድም ዐተሩን ወሰደ፡፡
ሲስማማ ነው እንጂ የሰው ልጅ ኵራቱ
መፋቀር ከሌለ ብዙ ነው ጒዳቱ፡፡
ታላቅ በጌትነት በገንዘቡ ኰርቶ
ወንድሙን ሊጐዳ በጥጋብ ተነሥቶ
አህያን ባያርደ ታናሽ ተቈጥቶ
ብድሩን ሊመልስ ቂሙንም ሊወጣ
ይህን ሁሉ ጒዳት ኋላ ባላመጣ፡፡
እብሪትና ክፋት የሚያመጡት ዕዳ
አያልቅም ይባላል ቢቀዳ ቢቀዳ፡፡
ብትንቁት እንኳን ቂሙን ባትፈሩ
ሰዎች በማንም ላይ ክፉ ሥራ አትሥሩ፡፡

# ጥበብ።

ያቺን ትንሽ ፍጥረት ንብን ተመልከት፤
አታሳልፈውም ጊዜዋን በከንቱ።
ትመላለሳለች ገደል ሳትል ሜዳ
አበባ ልትቀሥም ውሃ ልትቀዳ።
ከደከመችና ከሠራች በኋላ
ተመጋቢ ሁሉ ማሯን እንዲበላ።
ጉንዳንን አስተውሉት ገበያተኛ መስሎ
ሁሉም ባንድ መንገድ ሲሄድ ተከታትሎ
እሱም ይዋትታል ዳገት ሳይል ሜዳ
ለኑሮው ሲጣጣር ሥንቁን ሲያሰናዳ።
ወፍም ትደክማለች ታያለች መከራ
ልጆቿን ልትቀልብ ጐጆ ልትሠራ።
ማንኛውም ቢሆን ጥበብ የተባለ
ሳይደክሙ የሚገኝ ምንም ነገር የለ።
የንቦችን ታሪክ አጥንተን ብናይ
ንብረትና ትዳር ሀብትና ሲሳይ
ለራሳቸው ሳይሆን ለግል ጉዳይ
መልካም አኗኗርን ለትውልድ ሊያፈሩ
በየበኩላቸው ይገርማል ሲሠሩ።
ሕግን በመጠበቅ ሥራት ሲፈጽሙ
ለጋራ ቤታቸው አንድነት ሲደክሙ
ለግል ኑሯቸው ምንም አያስቡ፤
እያንዳንዱ ዜጋ ጠንክሮ በልቡ
የመንግሥቱንና የትውልዱን ክብር
ከምንም ነገር ጋር ሳያወዳድር
ከፍ አድርጎ በጣም ስለሚገምተው
ይህንን ዐላማ ሌትና ቀን ሳይተው

አስተውሎ ስለሚያይ በጣም አተኵሮ
መበለጥ አያውቅም ስለ ራሱ ኑሮ።
በሙሉ አካላት በእግሩም ሆነ በእጁ
ራሱን ሊሠዋ ይሆናል ዝግጁ
ጭንቅን ባለመሸሽ ምንም ባለ መፍራት
የተሰናዳ ነው ለመሞት ለመሥራት።
መሆናችን ቀርቶ ሁሉን ነገር ናቂ
ሆነን በመገኘት ጥበብን አድናቂ
የእነሱን አኗኗር ታሪክና ዜና
ጠልቀን ብንማረው ተግተን ብናጠና
ጨርሰን ሳናውቀው ሳይገባን የኖረ
እጅግ ብዙ ነገር እንማር ነበረ።
ይህን ብርቱ ጠባይ ይህን ሁሉ ጥበብ
ይህን ሁሉ ዘዴ ዐውቀው ለመሰብሰብ
ይህን ፍልስፍና ይህን መልካም ተግባር
ስንት ዘመን ይሆን የፈጁት ለመማር?
ይች ትንሽ ነፍሳት ምስኪኗ እንስሳ
እንደዚህ ስትሆን ግብሯን ሳትረሳ
ሰዎች ሆይ እናስብ እንዴት ነን እኛሳ?
ከኛ ግብር ጋራ በሚዛን ገቢታ
አስተያይተናል ወይ የእነሱን ሁኔታ።
መንግሥቱን ጠንካራ ለማድረግ ሲጥሩ
ተመራምረናል ወይም ምን እንደሚሠሩ?
ስለ ግል ስንፈልግ አለ ብዙ ዳኛ፤
በሥነ ፍጥረት ውስጥ አብነት ምሳሌ
ይቻለን የለም ወይ ለማግኘት ባያሌ
ተነሡ እባካችሁ ስለዚህ ድከሙ፤
ሊቃውንት በመጽሐፍ የሚሉትን ስሙ

ትጉ፥ ሥሩ ልፉ፥ ለሥልጣኔ አስቡ፥
ጥበብን ፈልጉ መጽሐፍን አንብቡ።
መጽሐፍን አንብቡ ከሁሉም ይልቅ
ቢቀዳ ቢቀዳ ጥቅሙ የማያልቅ።
መጽሐፍ ፀሐይ ሆኖ ሁሉንም ዕውቀት
አብርቶ ያሳያል ለሚፈልጉት
መጽሐፍ ዐይናችሁ ነው የልብ መብራት
ደግና ክፉውን የምትለዩበት።
መጽሐፍ ቃል ኪዳን ነው ሁሉን የሚያለማ
ሰውን የሚያፋቅር ሕዝብን የሚያስማማ
በመጽሐፍ ትርጉም ነው በቃሉ ምሥጢር
ነፍሳችን ራሷን የምትመረምር።
ይገባል ስለዚህ ለማግኘት ጥበብ
በያይነቱ መጽሐፍ ተጽፎ ለሕዝብ
ትርጉሙን ማጠጣት ቃሉን መመገብ።

## ሰውና ታሪክ።

ንጉሥም ዐዋቂ ጐበዝም አርበኛ
ሀብታምም ነጋዴ የሕዝቦችም ዳኛ
ሁሉም ባለው ሙያ በተቻለው ጉልበት
ክብሩን ለማጋነን ብዙ ዘር ለማግኘት
ስሙ ለዘለዓለም በዓለም እንዲጠራ
ይኖራል ሲደክም ሲጣጣር ሲሠራ።
ሞትም በብኩሉ የጭካኔው ብዛት
በሰው ላይ የሚሻው ሕይወቱን ለማጥፋት
ነፍሱን ለመነጠል ሥጋውን ለመቅበር
ብቻ ቢሆን ኖሮ እንዴት መልካም ነበር።
ሞት ግን በሰው ልጅ ላይ እጁን ሲዘረጋ

ከዚህ የበለጠ ያመጣል አደጋ።
ተስማምቶ የሚኖር ወገን አሳጥቶ
ስምን የሚያስከብር ምትክ ልጅ ነሥቶ
በቀሪው ገንዘብ ላይ ጠላት አስነሥቶ
ንብረቱ ፈራርሶ ከብቱ እየባከነ
ገንዘቡም ወገኑም እየተበተነ
መታሰቢያ ሆኖ የሚተላለፍ
ሰው ከሠራው ሥራ ምንም እንዳይተፍር
ቋሚ ሆኖ እንዳይኖር ዘርም ሆነ ዝና
ሁሉንም አንድነት ያደርገዋል መና።
ስለዚህ የሰው ልጅ ሞትን ለማሸነፍ
መታሰቢያ እሚሆን ጥቂት ነገር ሊያተርፍ
ዕድሜውን ይፈጃል ሲጥር ሲታገል
ሲለፋ ሲዋትት ድካም ሲቀበል
የሰው ልጅ ያስባል በገንዘብ በክብር
መታሰቢያ አድርጎ ስሙን ለማኖር
ሞት ግን ይጣጣራል ተረስቶ እንዲቀር።
ዐይናማ ተመልካች ይህን ጠብ ሲያስተውል
ሁል ጊዜ አሸናፊ ሞት ሲሆን ያያል።
እንሆ ስለዚህ ብዙ ልጅ በመውለድ
ገንዘብ ለመሰብሰብ በመውጣት በመውረድ
እስከ ብዙ ትውልድ የሚተላለፍ
ብዙ ወገንና መልካም ስም ማትረፍ
በደንቆሮ ሐሳብ የሚቻል መስሏቸው
የታሪክን ባሕርይ ባለማወቃቸው
መታሰቢያ እሚሆን ለመፈጠራቸው
ታሪካዊ ሥራ አንድ እንኳን ሳይሠሩ
ስንት ሕዝቦች ናቸው ተረስተው የቀሩ።

ታሪክ ለማቋቋም ስምን ለመትከል
ሰው በልደትና በሞት መካከል
ይገባዋል ብለው ምን ሥራ መፈጸም
ይህንንም ዐውቀው ለዚሁ በመድከም
መልካም የሚመኙ መልካም የሚያስቡ
ብሩኮች የሆኑ ካምላክ የተቀቡ
የሚጥሩ ሰዎች ለዚህ የታጠቁ
በጣም ጥቂት ናቸው እንደ አልማዝ እንደ ዕንቁ።

# ሕይወት እንቅልፍ ነች።

ዓለም ዓለም ሲሉሽ ስምሽ ደስ ያሰኛል፤
ግን ካንቺ የከፋ ምን ነገር ይገኛል።
ሕግሽ ጠማማ ነው ዘመንሽ ጠቋራ፤
ክብርሽ ልክስክስ ነው ደስታሽ መራራ።
ስንቱ ተታለለ አንቺን የሚመኝ፤
እውነትሽ ሐሰትሽ በውል አይገኝ።
ቃልሽ ወላዋይ ነው ግዝትሽ ይከዳል፤
ብይንሽ ዕውር ነው ፍቅርሽም ይጐዳል።
አኔን የሚገመኝ አወይ አንቺ ዓለም
ይኸ ሁሉ ሲሆን የሚጠላሽ የለም።
ያላንዳች ምክንያት ባማሽም አይበጅም፤
ሥራሽን ገልጬ ልናገረው እንጂ።
የዳኛ ቀማኛ ቂል የድኻ ብልኀ
ያዋቂ ገልጃጃ የሞኝ ብልኀተኛ
ያረመኔ መልካም የቄስ ዐመፀኛ
የችግረኛ ቸር የሀብታም ንፉግ
የወዳጅ ከሐዲ የባላንጣ ደግ
መኖሩን አስተውለን በዚህ ዓለም ላይ

ጠልቀን ስናስበው መርምረን ስናይ
በጣም የሚያስቸግር ምስጢር አለበት፤
ብልኅ ሰው ይራባል ሲተርፈው ደንቆሮ፤
ጐበዝ ሠራተኛ ሲሞት ተቸግሮ
ሰነፍ ይጨፍራል በጌትነት ሰክሮ።
መጻፍን አንብቦ ይህንን ሲያስተውል
ያልሠራ እንዳይበላ የሚለውን ቃል
እያየ ከመሣቅ ማነው ዝም የሚል።
አንዳንዱ ሰው ደግሞ ገንዘብ አለኝ ብሎ
በበታቾቹ ላይ ግፍ ሲሠራ ውሎ
ደስ ብሎት ይገባል ማታው ወደ ቤቱ፤
ብዙ ድኻ ደግሞ ገንዘብ በማጣቱ
ግፉን ተቀብሎ ባደባባይ ፊት
አልቅሶ ይቀራል አጥቶ ዳኝነት።
ነገሩማ ከጥንት እንደሚነገር
ዳኝነት የቆመው ለድኾች ነበር።
ከዚህ ሁሉ ደግሞ በጣም የሚብስ
የሰው ልጅ ሲወለድ ገና ሲፀነስ
አንዱ ልዑል ሆኖ አንደኛው ባላሊጋ
አንዱ ሀብታም ሆኖ አንዱ ባለጸጋ
አንዱ ድኻ ህኖ አንዱ ችግረኛ
አንዱ ዕውር ሆኖ አንዱ በሽተኛ
የበላይና የበታች ሆኖ ይወለዳል፤
አንደኛው ሲጠቀም አንደኛው ይጐዳል።
ከመውለድ በፊት መበላለጣቸው
በምግባራቸው ነው ወይስ በሥራቸው?
አንደኛው ሲታደል አንዱ ያልታደለ
ያ ምን መልካም ሠርቶ ይኸስ ምን በደለ?

ደግሞ ስንቱ ዋሽቶ ቀላምዶ ይከብራል፤
ስንቱ በውነት መንገድ ሥራውን ይሠራል።
እውነት በመውደዱም ተንቆ ይኖራል።
ይህን ሁሉ ካየን ባለም ላይ ሲሠራ
እኛም እንዲህ እንበል ከነቮልቴር ጋራ፤
ይች ዓለም ዐልጋ ነች፤ ዕድሜ ዕንቅልፍ ናት፤
ደስታም እልም ነው፤ ሐዘንም ቅዠት።
ይኽ ሁሉ ስሕተት ከእንቅልፉ ጋር አልፎ
ተገልጦ ሊታየው መልካምና መጥፎ
ፍጹም ከንቱነቷ ምድራዊ ደስታ
ከእንቅልፉ ይነቃል ሰው የሞተ - ለታ።

## ባልና ሚስት።

በተክሊል ተጋብተው ቁርበው የሚኖሩ
አንድ ሊቅ ሰውና አንዲት ሴት ነበሩ።
ከተጋቡ ወዲያው አንድ ዓመት ሳይሆን
ጠብና ጭቅጭቅ የሌለው መጠን
እየተፈጠረ በመካከላቸው
ሁል ቀን ጧት ማታ ስላበሳጫቸው
ምንም ቢቻቻሉ እንደዚህ ሊዘልቁ
የማይችሉት ነገር መሆኑን ዐወቁ።
የቍርባኑም ነገር ስለ ከበዳቸው
የመፋታት ሐሳብ ግራ ሆነባቸው።
ሽማግሌ ዘመድ ቄስም በነበሩ
ብልኀት ሲፈልጉ በብዙ መከሩ።
ሆኖም ባልና ሚስት ተክሊል ላያፈርሱ
በቄስ ተማምለው ተስማምተው ጨረሱ ፡
አብረውም ሳይኖሩ ተክሊሉን ለማክበር

የሚችሉበትን ብልኀት ይሹ ዠመር።
በኋላም ቤታቸው ለየብቻ ሆኖ
አኗኗራቸውም በደንብ ተወስኖ
ጋብቻቸው ሳይፈርስ ቤቱን ግን ለይተው
እንዳይለያዩ ሁለቱም ተስማምተው
በዚህ ዐይነት ዘዴ ይኖሩ ዠመር፤
ለመጫወትና ለመነጋገር
በፈለጉ ጊዜ አይችሉም ሁለቱ
ከኩል ሰዓት በላይ አብረው ሊጫወቱ።
ጥቂት እንደ ቈዩ ጠባቸው ይመጣል፤
ስለዚህ አንደኛው ተነሥተው ይወጣል።
ይልቁንም እሱ ጭቅጭቅ ትቶ
ገና ጠብ ሲነሣ ይኼዳል ተነሥቶ
ይህንኑ ፈርተው ከመጨቃጨቁ
ብዙ ጊዜ ኖሩ ለብቻ በሩቁ።
አንድ ቀን ባልዮው ታመመ ድንገት፤
በሽታውም ፈጥኖ ስለ ጠናበት
ሚስቲቱ ተጠርታ ስትደርስ እበር
ባሏን አገኘችው ሊሞት ሲያጣጥር።
ከፉኛ ደንግጣ እያዘነች ገብታ
ወደ ዐልጋው አጠገብ ቆመች ተጠግታ።
ከመሞቱ በፊት ቀና ብሎ አይቷት
ይኸውልሽ እኀቴ ተመልከቺ አላት፤
እንደዚህ ነውና ጥንቱን የለመደው
አንቺ ስትመጪ እኔ መሄዴ ነው።

# አንበሳና ጦጣ።

አንድ ቀን ተጣልተው አንበሳና ጦጣ
እጅግ ናቅሽኝ ብሎ አንበሳ ተቆጣ።
እጅግ አለመጠን ጥጋብ አብዝተሻል፤
ላታመልጪ መሸሽ ምን ያደርግልሻል።
ጥርሱን እያሳየ ጥፍሩን እያወጣ
ነይ ወዲህ እያለ ፈለገ ሊቀጣ።
ጦጢትም ተናዳ ከመሬት ሳትወርድ
ከዋርካ ላይ ሆና ስትንጐራደድ
እንደማይችል ዐውቃ ዛፍ እንደማይወጣ፤
እንዴት ትችላለኸ እኔን ልትቀጣ
ላንተ የሚገዙ ተኵላና ሥሥ ናቸው፤
ብንፈልግ ሄደኸ እነሱን ቅጣቸው።
አትችልም በኔ እንዲህ መንቀባረር
አያለች በድፍረት ትናገረው ዠመር።
ጠብቂኝ አለና ጌታው አቶ አንበሳ
ፎክሮ እየዛተ ሄደና እያገሣ
ሲጨልም ጠብቆ አድፍጦ ሊይዛት
ከምታድርበት ውስጥ ተቀምጦ ጠበቃት።
እያሰላሰለች ነገሩን አስታውሳ
ጦጢት ወደ ቤቷ ሄደች ሳትረሳ።
ከቤቷም አጠገብ ትልቅ ዛፍ ላይ ቆማ
ቤቱ ቤቴ ብላ ጠራቸው ደጋግማ፤
አግኝቶ ይሆናል አንድ ክፉ ነገር
ዱሮ ቤቴ ስለው አቤት ይለኝ ነበር።
ለተንኰል መሆኑን ሳያስብ ጨርሶ
አቤት ብሎ ጮኸ አንበሳው መልሶ።
ይህን ጊዜ ጦጢት የልቧን አድርሳ

ስታውቀው ከቤቷ መግባቱን አንበሳ
እደርበት ብላው ሄደች ተመልሳ።
ከትልቅ ኀይልና ከብዙ ጉልበት
ምንም ትንሽ ቢሆን ይበልጣል ብልኀት።
እንቅልፍ የተሠራው ለጨካኝ ደመኛ
አንተን ለመሰለ ለከፉ ዐመፀኛ
መቼ ሆነና ነው ብላ በመመረር
ዘመዷ የሆነች ሰምታ ስትናገር
ቀርባ እኅቴ ሆይ አንቺም አንዲት ዐይጥ
ድምጥሽን አጥፍተሽ እንደ መቀመጥ
የተናገርሽውን አሁን ቢሰማሽ
ትቀሪ ነበረ አንቺም ተበልተሽ።
ሞት እንዳይመጣብን እኛም እንዳንጠፋ
መቀስቀስ ይቅርብን ድመት ሲያንቀላፋ
እያለች ዘመዷን ድመት ሲያንቀላፋ
እያለች ዘመዷን በምክር አስረድታ
ይዛ ሄደች አሉ በግድ ጐትታ።

## ሥራ።

እንደ ሐምሌ ሌሊት ጨለማውን ለብሶ
በኖረበት ዘመን ድንቍርና ነግሦ
ግማሹ ተቀምጦ ግማሹ ሲሠራ
እኩሉ ሲገብር የቀረው ሲኰራ
በደልና ግፍም ከባድ ሸክም ሆነው
በድኻ ጫንቃ ላይ ሲኖሩ ተጭነው
ይህን በመሰለ በጨለማ ዘመን
ሠራተኛ ወድቆ ሰነፍ ሲመሰገን
ትጥቅን አሳምሮ መልክን ማቅለጥለጥ

ዐጀብ እያበዙ ጭፍሮቹን ማስሮጥ
ፊት እያጠቁሩ ጠግቦ መሣለቅ
ተረትና ቧልት ጨዋታ ማወቅ
ምላስ እንዳመጣ በድፍረት መናገር
እንደ ሦስት ዓመት ልጅ ደርሶ መንቀባረር
እኔ እገሌ ልጅ ብሎ መዛናት
የምድረ በዳ አውሬ ገድሎ መቀባት
ጀብዱ እየቆጠሩ ፎክሮ መግባት
ከሙያ ተቁጥሮ ከትልቅ ቁም ነገር
ማዕርግ እያገኙ ይሾሙበት ነበር።
ኋላ ግን ውሎ አድሮ ዘመን ሲተላለፍ
ድንቍርና ሲያረጅ ሥልጣኑን ሲገፈፍ
በስፍና ሕመም ደሙ ተመርዞ
በድንቍርና ሐብል እጁ ተገንዞ
ጊዜን እየፈጁ ሕይወትን መጨረስ
ሞት መሆኑን ዐውቆት አእምሮው ሲመለስ
በአርኣያ ሥላሴ ለተፈጠረ ሰው
ኀይል የሚሰጥና ክብሩን የሚያድሰው
ትልቅ ዋጋ ያለው በውነት የሚከበር
ትልቅ ዋጋ ያለው በውነት የሚከበር
ፍሬ የሚያፈራ ካንድ ሙያ በቀር
ሌላው ሁሉ ከንቱ መሆኑ ታወቀ፤
እሱም በዚህ ዓለም እያንጸባረቀ
ይኖራል ዘላለም እንደ ተደነቀ።
ካለም ነገር ሁሉ ዋጋው የበለጠ
እስከ አጥናፈ ምድር ዓለምን ያጌጠ
ለመሬት የሰጠ ውበትና ጸዳል
ክብርና ማዕርጉ ከሁሉ ይበልጣል፤

ያገኘውን ነገር በጁ ሲነካው
ሁሉ ያለ መልኩ መልክ የሚሰጠው
በመሬት ያሳያል የጥበብ ታምር
በልጦና አሸንፎ ከብሮ የሚኖር።
ሀብቱ ሁሉን በልጦ ከሁሉ ሲልቅ
ትሕትና ነው እንጂ ኵራት የማያውቅ።
በድን የነበረው የማይላወስ
በሱ ነፍስ ዘርቶ የሚንቀሳቀስ
ያደነዘዘውን ሕማመ ስንፍና
ይመልስለታል ብርታትና ጤና።
የሰፈረበትን ዕንቅፋት ጨለማ
ያጐናጽፈዋል የብርሃኑ ግርማ።
ስሙ ምን ይባላል ብለኸ ብትጠይቅ
ሥራ የሚባለው መሆኑ ዕወቅ።
ባለ ቅኔ ሞልቶ ባገሩ ቢነዛ
መነኵሴው በርክቶ መናኙ ቢበዛ
እልፍ አእላፍ ቢሆን ጐበዙ ሲጠራ
ሀብታሙም ድኻውም ጥበብን ሊያፈራ
ሁሉ እኩል ተዋርዶ ትክክል ካልሠራ
መልካም ኑሮንና ሥልጣኔን ቢመኙ
የውሃ ሽታ ነው መቼም አይገኙ።

# ንግሥት አግሪፒና።

ንግሥት አግሪፒና የኔሮን እናት
የተለየ ፍቅር ሳላደረባት
ልጅዋን አለመጠን ትወደው ነበር፤
ብዙ ሊቃውንቶች ገብተው በምሥጢር
ልጅሽ አንቺን ገድሎ ይነግሣል የሚሉ
ክፉ ትንቢት አለ ተጠንቀቂ እያሉ
ሲመክሯት ይህ ትንቢት አልመስል ቢላት
ልጄ ይንገሥ እንጂ እኔ እንኳን ብሞት
ምንም ቅር አይለኝ እያለች ስትኖር
የተባለ ነገር ሳይሆን እንዳይቀር
ንግሩም እንዲደርስ ንግሥት አግሪፒና
በሕይወት ቈይታ ልጅዋም አደገና
ለብቻ እንደ ልቡ ደልቶት እንዲኖር
መንግሥቱን ከናቱ ቀምቶ ሊያስቀር
እሷንም ለመግደል ቊርጥ ሐሳብ አድርጎ
ከወታደሮቹ ጨካኙን ፈልጎ
ሂድ እናቴን ግደል አለና ስደደው፤
የተላከው ሎሌ ኔሮን እንዲወደው
ሰተት ብሎ ገብቶ አንዴ እንደ መታት
ያ ትንቢት መድረሱ ትዝ ስላላት
ራሴ ምን አጠፋ ሆዴን ምታው እንጅ
ፀንሶ የወለደ ኔሮን ብሎ ልጅ
አለችው ይባላል ምስኪኗ ንግሥት
እንደ እባብ በዱላ ተወግራ ስትሞት።

# የሰማይ ጉዞ።

ጥበበ ተሰውራ ሆነና ደንቁሮ
ብዙ ሺ ዘመናት በመሬት ላይ ወድቆ
ይኖር የነበረ ዐፈር ላይ ተጣብቆ
ያዳም ልጅ አደገ አማረበት በጣም
መኖርም ዠመረ ያለብዙ ድካም።
እያደገ ሄደ እየገሠገሠ
ቁመቱ ተስቦ ኮከብ ላይ ደረሰ።
አደገ ከፉኛ በውቀት ቁመና
ገባ ወደ ሰማይ አልፎ ከደመና።
ለሥነ ፍጥረትም እሱ ሆኖ መሪ
ለመሆን ተነሣ ሰማይን መርማሪ።
ሊፈጸም አሰበ ያየርን ግሥገሣ፤
በውነት ልቡ ቈርጦ ጨክኖ ተነሣ።
ይህን ታላቅ ጉዞ በሰማዩ ሜዳ
ዛሬ ሊያከናውን ቈርጦ ሲሰናዳ
ዐቅዱን አደራጅቶ ንድፉን ሲዘረጋ
መነሻ መድረሻው አልፋና ዖሜጋ!
ትንግርት በሆነው በዚህ ሩም ጉዞ
ባየር ሲወረወር ጥበብ ተመርኵዞ
ሥራውን ሲፈጽም በመዘዋወሩ
የድንኳን መትከያው ኮከብ ነች ሰፈሩ።
ፀሓይ፥ ኮከብ፥ ፕላኔት፥ በዚያ በሰፊ አገር
አያሌ ሚሊያርድ ቍጥራቸው ቢሰፈር
ሰው መሬትን ለቆ ከኮከቦች መካከል
ከፀሓዮች ጋር ገብቶ ሲቀላቀል
በጥበቡ ድፍረት መንፈሱ እየፈላ
እሰፊው ዓለም ውስጥ ከገባ በኋላ

ዘልቆ ሲያከናውን ታላቁን ምርመራ

ተግባር ሊፈጸም ነው በውነት የሚያኰራ።

የረቀቁ ሰዎች በጥበብ ያደጉ

ከሰማይ ላይ ወጥተው ይህንን ሲያደርጉ

ሰነፎቹ ሰዎች በውቀት ያልከበሩ

ተፈርዶባቸዋል እዚሁ እንዲቀሩ።

ከሰማዩ በታች ካየር ከደመና

ከዚህ ወዲአይ ቅጣት አይገኝምና።

ውሳኔ ተደርጓል እንዲከለከሉ፤

የሰማዩ ጉዞ እንዳይካፈሉ።

================

ምናልባት ምናልባት ገና ተርፎ ስፍራ

እስቲሄዱ ድረስ እነሱም በተራ

እስኪታወቅ ድረስ የጉዞው ከሳራ።

# ሙሴ።

አልፍሬድ ደ ቢኚ ከፈረንሳይ ዋናች በለቅኔዎች አድኑ ነው። እሱም በያይነቱ ብዙ ግጥሞች ጽፏል። ከነዚህም ግጥሞች አንዱ «ሙሴ» የተባለው ነው። ሕዝበ እስራኤልን ፈርዖን ጭኖባቸው ከነበረው የባርነት ቀንበር ነጻ ባወጣቸው ጊዜ ሙሴ ብዙ ድካም ደርሶበታል። ከፈርዖን ጋራ ያን ያኸል ትግል አድርጎ ነጻ ካወጣቸው በኋላ በምድረ እብዳ ደግሞ አርባ ዓመት ሙሉ እየመራቸው እግዚአብሔር ለአብርሃም ቃል ገብቶለት ወደ ነበረችው አገር እስቲያደርሳቸው ድረስ የእግዚአብሔርን ሕግ እየጣሱ የእሱንም የመሪያቸውን ትእዛዝ እያፈረሱ በጣም አበሳጭተውታል። የሕዝብ መሪ መሆን የቱን ያኸል አድካሚ ሥራ እንደ ሆነ ከማንም ይልቅ የቀመሰው ሙሴ መሆኑ አይጠረጠርም። ስለዚህ እንደ አልፍሬድ ደቪኚ አሳብ በመጨረሻ ጊዜ ሙሴ ይህ የሕዝብ መሪነቱ ተግባር በጣም ስለ መረረው ሞቱን እስከ መመኘት ደርሷል። በውነተኛው ነገር የሆን እንደ ሆነ ሞቱን የተመኘ ሙሴ ብቻ ነውን? እንኳንስ ያን ያኸል በትግል ማዕበል ተውጦ በኖረው በሙሴ ሕይወት ላይ ይቅርና እያንዳንዳችንም ብንሆን በኑሯችን ውስጥ መከራና ብስጭት ሲገጥመን ብዙ ጊዜ ሞትን የምንመኝበት ሰዓት አለ።

አልፍሬድ ደ ቪኚ ይህ ጉዳይ በመረመረው ጊዜ ብልኅ በመሆን ሰው የሚያገኘው ደስታ በሐዘን የተለወሰ መሆኑን ተገንዝቦታል። ሰዎች በመልካም ዕድሉ የሚቀኑበት እንደ ሙሴ ያለ ማንኛውም ትልቅ ሰው ቢሆን ለሌሎች የሚመስላቸውን ያኸል በልቡ ውስጥ ደስታ እንደ ሌለ ገምቶታል።

ከዚህም ሌላ ይልቁንም አልፍሬድ ደ ቪኚ በሙሴ ስም አድርጎ የገጠመው ይህ ግጥም እሱው ራሱ ይህንኑ የመሰለ ብስጭት የሚያጠቃው ሰው ስለ ነበረ ይህንኑ ለመግለጥ የጻፈው መሆኑን የግል ኑሮውን ታሪክ የመረመሩት ሰዎች አረጋግጠውታልና። ይህ ባለ ቅኔ የሰዎችን ክፋትና ተንኰል፤ የመሠሪነታቸውን ምስኪንነት በማስተዋል ስለ ሰዎች ጠባይ እጅግ ያንዝ እንደ ነበረ ታውቋል። ወደ ራሱ ጉዳይ ተመልሶ ሲመለከት ደግሞ የሰዎችን ጠባይ ለማሻሻል በመፈለግ ይህ የሚደክምበት የደራሲነት ተግባር ምንም የማይጠቅም መስሎ ስለ ታየው ሙሴን አመካኝቶ ሞቱን ከእግዚአብሔር ለመነ። ባጭሩ አልፍሬድ ደ ቪኚ በዓለም ላይ የሚመለከተው ነገር ሁሉ ከንቱነት ብቻ ሆኖ ታየው።

እኛሳ፥ የሰው ልጆች የሆን ሁሉ ይህን የመሰለ አሳብ አልፎ አልፎ ጥቊር ደመና እየሆነ በነፍሳችን ሰማይ ላይ በመመላለስ የሚመጣበት ጊዜ መኖሩን እንክዳለንን? ይህን ቅኔ በምንመለከትበት ጊዜ በስሜታችን ውስጥ የሌለው ነገር ነው ያቀረበልን ብለን አልፍሬድ ደ ቪኚን የምንዘልፈው አይመስለኝም። መቼውንም ቢሆን ባለቅኔ ማለት በሁላችንም ላይ ያለውን ነገር አፈ ጉባኤ ሆኖ ይናገራል እንጂ፤ በሰው ላይ የሌለውን ነገር አይፈጥርም።

ይኸውም የተባለው የአልፍሬድ ደ ቪኚ ቅኔ እንሆ ከዚህ ቀጥሎ የምናቀርበው ነው።

እግዚአብሔር ፊት ቆመ ሙሴ ቀረበና፤

ንግግር ዠመረ ሸፍኖት ደመና።

ለእግዚአብሔር አለው እኔ አይበቃኝም ወይ?

ደግሞ ወዴት ልሂድ አሁን ጌታዬ ሆይ?

አምላኬ አኖርከኝ አድርገኸ ኀይለኛ፤

ተወኝ ወደ መሬት ገብቼ ልተኛ።
በምኔ መረጥኸኝ በየትኛው ሥራ፤
ሕዝብኽን መራሁት ወደ አዘዝከኝ ስፍራ።
እግሩም ይኸው ቀርቧል አገሩን ሊነካ፤
እንግዲህ ስለ እኔ ሌላ ሰው ይተካ።
የምትሾመውን ሰው በቶሎ ምረጠው
የያዝኩትን ሥልጣን ለቅቄ አገሩን ይተካ።
የምትሾመውን ሰው በቶሎ ምረጠው
የያዝኩትን ሥልጣን ለቅቄ እንድሰጠው።
የኔን ተስፋ ሁሉ አታድርገው መና፤
መልስኽ አኑረኝ በሰው ድንቅ፡ርና።
ከኮሬብ ተራራ እስከ ኔቦ ድረስ
ሕዝበ እስራኤልን ይኸው ባንተ መንፈስ
ስመራው በልቤ ብፈልግ ብመኘው
ከቶ መቃብሬን አልቻልኩም ላገኘው።
የብልኆች ብልኅ ሆኘ ባንተ ሥራ
ኖርኩኝ ይህንን ሕዝብ በጣቴ ስመራ።
የእሳት ዝናም ጥዬ ነገሥታቱን ቀጣሁ፤
ለብዙ ትውልዶች አዲስ ሕግ አወጣሁ።
አያሌ ነገዶች በእግሬ ተረገጡ
አያሌ ነገዶች በእግሬ ተረገጡ
ትውልዶች ተይዘው በእጄ ተቀመጡ።
አምላኬ አናርከኝ አድርገኝ ኀይለኛ
ተወኝ ወደ መሬት ገብቼ ልተኛ።
የላይ ምስጢር ሁሉ ለኔ ተገለጠ፤
ኃይልህ ባይኖቼ አድሮ ሰው አንቀጠቀጠ።
ገፍፌ እጥላለሁ የሌቱን ጨለማ
ድምፄም እስከ ሰማይ ዘልቆ እየተሰማ

በስሟ ስጠራት እያንዳንዷ ኮከብ
«አቤት» ትለኛለች በሰጠኸኝ ጥበብ።
እጄን ስዘረጋ በደመናውም ላይ
ዝናቡ ይደርቃል አይወርድም ከሰማይ።
ከተሞች በኔ ቃል በመሬት ተዋጡ፤
ተራሮች በነፋስ ተገለባበጡ።
የማይደከመው እግሬ አይበቃውም አገር
ውሃው ገለል ይላል ባሕሩን ስሻገር።
ድምፄንም ሲሰማ ጭጭ ይላል ባሕሩ
አዲስ ሕግ ሲሻ ሕዝቤ ለምግባሩ፤
ናላዬን ሳደርገው ወደ ሰማይ ቀና
መንፈስኽ ይወርዳል በኔ ላይ ያድርና።
መድረሻ ታጣለች መሬቷ ተናውጣ፤
ትሸፋፈናለች ፀሓይም ደንግጣ።
መላእክት ቀኑብኝ በያሉበት ቦታ፤
ይኸ ሁሉ ሲሆን በያሉበት ደስታ።
አምላኬ አኖርከኝ አድርገኝ ኀይለኛ፤
ተወኝ ወደ መሬት ገብቼ ልተኛ።

# ትሕትና።

ከሰማይ ደመና ከላይ ተለይታ
ወደ ታች የመጣች የዝናም ጠብታ
የተዘረጋውን ውቅያኖስን አይታ
እንዲህ ተናገረች ለፈጣሪ ጌታ፤
እንደምን ታላቅ ነው ያምላክ ቸርነቱ
የፈጠረው ባሕር የያዘው ስፋቱ
ግምቱ ይከብዳል ለፍጡር አእምሮ፤
ይልቁንም ደግሞ ይህን ሁሉ ፈጥኖ
እኔን የመሰለች በጣም ትንሽ ነገር
ማሰቡ ደነቀኝ አንድነት ለመፍጠር።
ከታላቁ ቦታ ወጥቼ ከሰማይ
ወርጄ ከመሬት ወድቄ ባሕር ላይ
ጠፍቼ እቀራለሁ በፍጹም ጨርሼ
አልገኝም በቃ ዳግም ተመልሼ።
እኔ ተፈጥሬ በዚህ ግሩም ያንተ ሥራ!
እንደዚህ እያለች ወርዳ ከምድር
ደረሰች በቅጽበት እባሕሩ ዳር
ከፍቶ የጠበቃት አፉን ፊት ለፊት
ተቀብሎ ዋጣት የዛጐል ቅርፊት
እንደ ተሸነፈች ከቅርፊቱ ገብታ
ብዙ ዘመን ሙሉ በውስጡ ቈይታ
ተለወጠችና በሥነ ፍጥረቷ
ዕንቍ ሆነች አሉ አማረ ውበቷ።
መልኳ እያበራ በማንጸባረቁ
ሰዎች አዩዋትና በጣም ተደነቁ።
ወስደው እንደ ደንቡ እንደ ዓለም ልማድ
ጌጥ ሆነች ይባላል ለነገሥታት ዘውድ።

ትሕትና ብታሳይ የዝናብ ጠብታ
ይህን ፈጸመላት የሰማዩ ጌታ።
በእግዚአብሔር ቸርነት በፈጣሪ ጸጋ
ሁል ጊዜ ትልቅ ነው የትሕትና ዋጋ።

# የተኛ ሰው።

ጥሩ ምግብ በልቶ ጥሩ ጠጅ ጠጣ፤
ከመጠን ያለፈ ጠገበ እስካንገቱ፤
ድካም ተጫጭኖት እንቅልፉ ቢመጣ
አውልቆ እያዛጋ ተኛ ባለቤቱ።
መብራቱ ጨለመ የሰው ድምፅም የለ፤
ጨርሰው የዘጉት የሌለበት ጌታ
ወፍ የማትዞርበት ወና ቤት መሰለ፤
ግቢው ጭር ብሏል በታላቅ ጸጥታ።
አጥሩም ይታያል አልፎ አልፎ ፈራርሶ፤
ዳር ዳር እየዞረ ይሰልላል ሌባ፤
አልደፈረም ገና አለመጣም ጨርሶ፤
ቆሞ ያመነታል አስቦ ሊገባ።
ጥጋብ የተሰማው ደከሞት ሲያንቀላፉ
የራበው አድብቶ ይፈልጋል ጊዜ
ሰዓቱ ሲመቸው ሊቀማ ሊያጠፉ፤
ወንበዴ ይነሣል ለጌቶች አባዜ።
ዐወቀ እንደሌለ በግቢው ዘበኛ፤
ውሾችም አይጮኹ ሰውም አይናገር፤
ባለቤት ቢኖርም ዐወቀ እንደ ተኛ፤
እንግዲህ ለመግባት ምንም አይቸገር።
ቊልፉን ጠመዘዘ በሩን ነቀነቀ፤
ከሳንቃው ታገለ በዘዴ በርጋታ

መሰርሰሪያ አግብቶ በሩን ፈለቀቀ፤
ቍልፉን ተከፈተ ለቀቀ ባንድ አፍታ።
በእጁ እየዳበሰ በዘዴ በመላ
ከፊቱ ሰው ቢያገኝ በጩቤ ሊወጋ
ገባ እያዳመጠ ሌባው እያሰላ
ወደ መኝታ ቤት ቀረበ ተጠጋ።
እንቅልፍ ተጭኖታል ከርሳስ የከበደ፤
ባለቤት ይቃዣል መንፈሱ ታውኮ፤
ዳር ግን አልነቃም እየተኛ ሄደ፤
ሥጋ ወድቋልና በድካም ተማርኮ።
ገንዘብ ይፈለጋል መኝታ ቤት ገብቶ፤
ዕቃ ይነካካል በእጁ እየዳበሰ፤
ሊወጣ አልወደደም ምንም ቢሆን ከቶ፤
ፈልጎ ሳያገኝ ከሺ ብር ያነሰ።
መብራቱን አብርቶ ያማርጣል ዕቃ፤
ባለቤት አይሰማም ተጭኖታል ጠጁ፤
ሌባ ምን ቸገረው ቢነቃ ባይነቃ፤
የተሳለ ጩቤ ጨብጧል ቀኝ እጁ።
ዕቃው ይተራመስ ይመረጥ ይሰረቅ፤
የገባውም ሌባ ቤትክን ይበዝብዘው፤
እባክኽ ባለቤት ተኛ አትነቃነቅ፤
አትችልምና እንግዲህ ልትይዘው።
ጌታ ተወራጨ ዐልጋውም ተንጫጫ፤
ሌባ ደነገጠ ጆሮእውን አቆመ፤
እባካችሁ ሰዎች ጫኑበት ሙቀጫ
እየተኛ እንዲሄድ እየተዳከመ።
መንቃት ቀድሞ ነበር ሲደፈር አጥሩ
መንቃት ቀድሞ ነበር በሩ ሲሰረሰር

የገባ ጊዜ ነው ያለቀው ነገሩ፤
አሁንስ ተጋድሞ እግር እጅኽ ይታስር።
እግር እጅኽ ይታሰር ጆሮኽም አይስማ፤
መንፈስኽ ይደንዝዝ ይዳከም በብዙ፤
ይገድልኽ የለም ወይ ከእንግዲህ ወዲያማ፤
ሊያጠፋህ ነው እኮ ጩቤውን መያዙ!
አውልቀሽ ተኙተኽ ሌባ ሰብሮ ገብቶ
ከእንግዲህ ወዲያ ደምኽ ከንቱ አይፍሰስ፤
ሌባ ከነጩቤው ካልጋኽ ተጠግቶ
አሁን ምን ይጠቅማል ያንተ መንቀሳቀስ።
ተኛ ደስ ይበልኽ በቅዠቱም ቦታ
ይሻላል ጥሩ ሕልም ከራስኽ ቢገባ፤
ሕይወትኽ ትቅርልኽ በገንዘብኽ ፈንታ፤
ይሥራ እንደ ፈቀደው የገባውም ሌባ።
የተፈራው ነገር አልቀረም ደረሰ፤
የታጨ ነውና ለዚህ ቀን አበሳ
ከቃዠ በኋላ ከተንቀሳቀሰ
ሰዎች እዘኑለት ባለቤት ተነሣ።

## የማይለወጡ ነገሮች።

በበጋ ወራቶች ትወጣለች ፀሓይ፤
ክረምትም ይበርዳል ዝናም እየጣለ፤
ሌሊት ያበራል ከዋክብት በሰማይ፤
ኗሪ ነገር ሁሉ ይኖራል እንዳለ።
ፈሳሽ ውሃ ሁሉ ቍልቍለትን ይሻል፤
የእሳት ጠባይ ሲሆን መሄድ እየጋለ
ጨለማ በባሕሪው ብርሃንን ይሸሻል፤
ኗሪ ነገር ሁሉ ይኖራል እንዳለ።

ዐዋቂ ያስባል ልጆች ሲጫወቱ፤
ውጊያ ይፈልጋል መሣሪያ የሳለ፤
ጐበዝ ያሸንፋል ደካሞች ሲረቱ
ኗሪ ነገር ሁሉ ይኖራል እንዳለ።
ጠቢብ ይጠቀማል ሆኖ የዓለም ጌታ፤
ሰነፍ ይዋረዳል ሳይሠራ የዋለ።
ሰው ሁሉ ይይዛል የምግባሩን ቦታ
ኗሪ ነገር ሁሉ ይኖራል እንዳለ።
አዲስ ትውልድ ሁሉ አላፊን ይንቃል፤
በሁሉም የምበልጥ እኔ ነኝ እያለ
ባባቱ ተግባሮች ልጅ ሁሉ ይሥቃል፤
ኗሪ ነገር ሁሉ ይኖራል እንዳለ።
ልጃገረድ ሁሉ ትሻለች እጮኛ
ባሕሪው የሚስማማት እሷም የመሰለ
ጥሩ ነገር ማየት አይወድም ምቀኛ
ኗሪ ነገር ሁሉ ይኖራል እንዳለ።
እናት ስለ ልጅዋ አንጀቷ ይባባል፤
ቅብዝብዝ ይሆናል ነፍስን የገደለ፤
ከክፉም ከደጉም የሰው ዘር ይረባል፤
ኑዋሪ ነገር ሁሉ ይኖራል እንዳለ።
ሁሉም እንደ ባሕሪው ሁሉም እንደ ባህሉ
ተፈጥሮ ጠባዩን እየተከተለ
ዘለዓለም ያው ሆኖ ሁሉም እንዳመሉ
ኗሪ ነገር ሁሉ ይኖራል እንዳለ።

# ነፋስ ይዞት ሄደ።

እብሪት አሉባልታ
እሮሮ ሰምታ
ወቀሣ ዘለፋ

ጭቅጭቅ ነቀፋ
ስድብና ስብቀት
ነገርና ንቀት
ተንኰልና ሤራ
መተትም ደንቃራ
መፋቀር መዋደድ
ምስጋና መዛመድ
ተግቶ መረዳዳት
ነቅቶ መጐዳዳት
ሰዎች ደክመው ደክመው
እንደዚህ ፈጽመው
የሠሩትን ሥራ
ደስታ መከራ

ትልቅ ነፋስ ነፍሶ
ሁሉን አግበስብሶ
ምንም ሳያግደው
ጠራርጎ ወሰደው።
ካፈሩ ከትሉ
ከሣር ከቅጠሉ
ከትቢያ ካቧራ
ከቆሻሻ ጋራ!
ከሠሩበት ቦታ
ሁሉንም አንዳፍታ
ጠራርጎ በመጣስ

ይዞት ሄደ ነፋስ!
ፍቅሩንም ጠቡንም
ሳያተርፍ ምንም
የደከሙበትን
አረገው ብትንትን!

## መስከረም ጠባ።

ዐቧራ ተነሣ ነፋሱ ነፈሰ፤
ደመና እየሸሸ ሰማዩ ሲጠራ
ስንዴ ጨበጨበ እሸቱ ደረሰ፤
ዝናቡ ሲፈጸም ተከተለ ብራ።
ካፋፍ ላይ ሲያስተውሉት አገሩን በሰፊ
መሬት ትታያለች የክት ልብሷን ለብሳ
ለምለሙ ውበቷ አይመስልም አላፊ፤
አረንጓዴው ቀለም ማማር የተነሣ።
እንግጫ ሰንበሌጥ ሰርዶና ቄጤማ
አክርማና ጦስኝ ደግሞም እነሙጃ
አበቃቀላቸው ኅቡር የተስማማ፤
መስኩ ላይ ተነጥፏል ያበባ ስጋጃ።
ቀለሙ ወይን ጠጅ የስጋጃው መልኩ
ቍጭ ብድግ እያለች ስትጫወት ወፏ
ሕይወት አገኘና ደስ ደስ አለው መስኩ፤
እጅግ ያማረ ነው ጥቍር ብጫ ክንፏ።
ውብ ዐደይ አበባ ምድሩን አለበሰው፤
ልጆች ተሰብስበው አሉ ሆያ ሆዬ፤
ያበቦቹ ሽታ አየሩን አደሰው፤
እኔም ደስ ብሎኛል ፍጥረቱን መስዬ።

# አንቲስቴኔ።

አንቲስቴኔ እሚባል የግሪክ ፈላስፋ
በውቀት የረቀቀ ትምህርቱ የሰፋ
ምግባራቸው ክፉ ስማቸው የጠፋ
የተጠሉ ሰዎች ሲያመሰግኑት
በጆሮው ሰምቷቸው አዘነ በውነት።
ስለምን ታዝናለኽ ሰው ሲያመሰግን
መመስገንም ክፉ ነው ትላለኽን?
ብለው ቢጠይቁት ሊቁ አንቲስቴኔ
ዛሬ ምር ማዘን ይገባኛል እኔ
ምን ክፉት አለበት መልካም ነው መመስገን፤
ጉዳዩን ላስተውለው ደግሞ ባንድ ወገን
እኔም እንደነሱ እንደ ክፉ ሥራ
አይተውኝ ይሆናል ምናልባት ስሠራ
እንጂ እኒህ ሰዎች ሌላ ምክንያት
እኔን ለማመስገን የሚችሉበት
ከወዴት አገኙ ብዬ በማለት
ስለ ጠረጠርኩት ራሴን በራሴ
በጣም ትልቅ ሐዘን ተሰማት ለነፍሴ
አለና መለሰ ትልቁ ፈላስፋ
ስለሚጠነቀቅ ዐመሉ እንዳይጠፋ።

# ሊቅና ባልተኛ።

በክብር፥ በማዕርግ ደልቶት የሚኖር
የንጉሥ አሺከሮች አንድ ሰው ነበር።
በዚያው በሱ ዘመን ደኸይቶ በጭንቅ
ተጕላልቶ የሚኖር ነበረ አንድ ሊቅ።

የንጉሡ አሜዋች ሊቁን ተናገረው
በምን ምክንያት ነው ወድቀኽ የምትኖረው?
እኔ እንኳ ማይምኑ ምንም የማላውቅ
አስሩን ለፍልፌ ሰውን በማሳቅ
ክብሬና ማዕርጌ ሀብቴም እየሞላ
ተመልከተኝ ስኖር በምቾት በተድላ።
ይህን ሰምቶ ሊቁ መለሰ እንዲህ ሲል፤
ጨዋታ የሚወድ አንተን ይመስል
ንጉሥ ስለ አገኘህ እውነት ደልቶኻል።
እኔም እንደዚሁ እግዚአብሔር ቢፈቅድ
እውቀት የሚፈልግ ጥበብ የሚወድ
ንጉሥ አገኝና እበቃለሁ ለክብር፤
አለዚያም እንዲሁ በማጣት በችግር
በመከራ ኖሬ ወድቄ አጥቼ
እጨርሳለሁ ዕድሜዬን ገፍቼ።

## አሪስቶት።

አሪስቶት የሚባል ፈላስፋው መምህር
ከሊቆች መካከል ቆሞ ሲያስተምር
የወዳጅን ነገር ጠቅሶ ሲነግራቸው
እንዲህ ሲል በምክሩ አስጠነቀቃቸው፤
ስሙኝ ልንገራችሁ ወዳጆቼ ሆይ
ምንም ወዳጅ የለ በዚህ ዓለም ላይ!

========

ለዚሁ ላሪስቶት ለትልቁ ሊቅ
ወዳጆችኽ ያንተን ዕውቀት በመናቅ፤
ሲያሙኽ ሰማናቸው፥ ብለው ቢነግሩት
እንኳን ማማትና እሌለሁበት

ቢደበድቡኝም አልቀየማቸው፤
አሚታ አይጐዳኝም ሲል መለሰላቸው።
እኛም እንደ አሪስቶ ባንሆንም ሊቅ
ይገባናል ዘወትር አሚታን መናቅ።

## ጥልቅ አሳቦች።

አጣሁ በለጡኝ ስል ለገንዘ ለክብር
መመረሬ ቀርቶ ሕያው እግዚአብሔር
በሙሉ ልቡና ደስ እያላት ነፍሴ
ስምኸን ጧት ማታ ታመስግን ምላሴ
ፈጠርኩኽ ስላልከኝ በአርኣያ ሥላሴ
ውለታን ካወቀ በውነት ሰውነቴ
በፊት ላመስግንሽ በሥነ ፍጥረቴ።
ለሥጋ እንኳ ኑሮ አለው ብዙ ጣጣ
ሠርቶ እሚበላበት ሰው እንጀራ እያጣ
ደግሞ ነፍሴ በላይ እንዳትንገላታ
ካሁኑ ዝምሮ ትገዛ ለጌታ።
የምድር ንጉሥ እንኳ ምስጢር ያስጠብቃል፤
የሚያወራውም ሰው በብርቱ ይቀጣል፤
ሕያው ሥላሴማ ምሥጢሩ የሰፋ
ሲመራመሩበት ምነው አይከፋ።
የዚህ ዓለም ሰዎች ይቀባጥራሉ፤
የሰው ሥጋ መብላት እርም ነው እያሉ፤
እንግዲህ ወደ ፊት እንዳትታለሉ
የሰው ሥጋ ሆኗል መድኀኒት ለሁሉ።
ፀሓይ ብርሃንሽን የመልክሽን ጸዳል
ተመልክተው ሲያዩት በብዙ ማስተዋል
በጣም ይናፍቃል የፈጣሪሽ አምሳል።

ቄንጦ፥ ጐበዝ ሀብታም፥ ዐዋቂ ተብሎ
ያዳም ልጅ በመሬት እንደ አበባ በቅሎ
አንድ እንኳን ሳይታይ ከመካከል ተርፎ
ሁሉም ወዳቂ ነው እንደ አባባ ረግፎ።
ለሁሉ ጊዜ አለው ይላል ሰሎሞን፤
እጠይቀው ነበር በተገናኘን፤
ሞት የሚሞትበት ጊዜው መች ይሆን?
የበረዶ ፍሬ ናት የኛ ሕይወት
ደመና ከሰማይ፥ የወረወራት፤
ሥጋ ከለበሰ ሰው ዓለም ላይ መጥቶ
በረዶም ከሄደ ደመና ወጥቶ
ወደ ዐፈረ መግባቱ አይዛባም ከቶ።
ሰው ከናቱ ማሕፀን ሲወለድ ተረግዞ
በሞት ጐዳና ላይ ይዠምራል ጕዞ።
ፊት ለፊት እያየው ትልቁን አደጋ
ልቡ ሲያፈገፍግ ዕድሜው ግን ሲጠጋ
ሲያውቀው በመሞቱ በጣም ይጨነቃል፤
መሸሻ በማጣት ቆሞ ይጠብቃል።
አደገ ከበረ ነገሠ ገነነ፤
ተቀጨ ደኸየ ተሰዶ በነነ፤
አጣ በለጠገ ቸገረ ተመቸው፤
ሰው አመሰገነ አማ ጠላ ተቸው።
ታደለ እበነ ተሾመ ታወቀ፤
ታረዘ ተጋዘ ተራበ ተናቀ።
አንዱ ምን ጐደለበት አንዱስ ምን ያተፋል፤
ችግርና ተድላ ሁሉም እኩል ያልፋል፤
ሰው ሁሉ ትክክል ይሞታል ይረግፋል።
ውስጠ ልቡናውን ራሱ መርምሮ

ኅጢአቱን ክፉቱን በሐሳቡ ሰፍሮ
ይህን ሁሉ በደል የሌለው መጠን
አድራጊና ሠሪው እሱ መሆኑን
ኅሊናው ተረድቶ ሲያስበው መንፈሱ
ምን ፍጡር ይገኛል የማታርፍ ነፍሱ?
መልሶ የማይንቅ ራሱን በራሱ?
አዳምና ሔዋን ባጠፉት ጥፋት
አምላክ አስወጣቸው ከምድረ ገነት፤
ሰው ረክሶ ቢገኝ እንደ እንስሳ ሁሉ
ሰዶምም ገሞራ እንደ ዕንጨት ከሰሉ።
ኃጢአት በርክቶ መጠን ቢያጣ ክፋት
እግዚአብሔር በውሃ ዓለም አጠፋት፤
ብዙዎች ነቢያት ሌት ተቀን ሳያርፉ
እስከ ጌታ ልደት ቃለ አብን ለፈፉ፤
ዐማኑኤል ወርዶ የሰው ሥጋ ለብሶ
ወንጌል አስተማረ ኦሪትን አድሶ፤
ይኸ ሁሉ ልፋት ሆነና በከንቱ
በኅጢአትም ሆነ ባመፅ በክፋቱ
ብሶበታል እንጂ ስትመለከቱ
ምንም አልተሻለው ሰው ከሰውነቱ።
ሰው በሥጋ በነፍስ ቆሞ በሕይወቱ
የሥጋን ደስታ ሲሆን ፍላጎቱ
ሊያገኛት አይችልም ከቶ ምን ቢሆን
ጨርሶ ካልጣለ የነፍሱን ወገን።
ሁለት ነገር አለው ሰው ሲኖር ባለም ላይ
መልካም ዐመልና አንድ ክፉ ጠባይ።
የሁለቱም ሥልጣን እያደር ይስፋፋል
ሰውም ባንዱ ለምቶ ባንደኛ ይጠፋል።

ያለውን ማጥፋፋት ገብታ በማይሆነው
ሁሉን ቅጥ ማሳጣት ለሷ ቁም ነገር ነው።
የምትሄድበትን ሳታውቀው ጨርሳ
ዕውሯን የምትሮጥ እንዲያው በዳበሳ
ሳትፈራ ሳትሠጋ ሳታስተውል አስባ
እያቅነዘነዛት ገደል የምትገባ
ዐውቃለሁ ትላለች ዕውቀቷን በታትና
ክልፍልፍ እብድ ነች እመት ድንቍርና፤
የጥፋቷ ብዛት ልክ የለውምና።
ብረትና ሸማ ቢጋጩ አንድነት
ከመካከላቸው አይወጣም ጨኸት።
ግን ብረት ለብረት አንድነት ቢማቱ
እርግጥ ነው ይገኛል ድምፅ ከሁለቱ።
ደንቁሮና ዐዋቂ አይስማሙም አሉ፤
እንደ ምን ይስማማ ሰው ያለመሰሉ።
ደግና ክፉውን እያደባለቀ
መንፈሱ ለይቶ ፍርድ ካላወቀ
ድካሙ ከሆነ ለጌጡ ለልብሱ
ልፋቱ ከሆነ እስኪሞላ ከርሱ
ካላቀርበለት ኅሊናው ወቀሣ
በምኑ ይበልጣል የሰ ልጅ ከእንስሳ።
አንዳንድ ሰው አለ መንፈሱ ደካማ፤
ደጋግመው ሲነግሩት ምንም የማይሰማ
ዘርዝረው ሲያስረዱት አዳምጦ ጨርሶ
ጥያቄ ያመጣል እስር ተመልሶ።
የዕውቀቱ መደንዘዝ ያሰኘዋል ከቶ
ውስጡን የሚሠራጭ በደም ሥሩ ሞልቶ
ቀዝቃዛ ውሃ ነው ደም መሆኑ ቀርቶ።

ገንዘብ ሰብስቦ የማይሰጥ ለሌላ
የብረት ሣጥን ነው ሀብትን የተሞላ
ከፍተው እንዳይወስዱ ቍልፉ የጠፋበት
ሀብቱም የሚገኘው የተሰበረ-ለት።
ድካሙ ምኞቱ ሐሳቡ መንፈሱ
ልቡ ሃይማኖቱ እምነትና ነፍሱ
ከተቀላቀሉ ከገንዘቡ ጋራ
ፍቅር ከሰው ልጅ ላይ ስሙም አይጠራ።
የተማረ ሆኖ ዕውቀቱን የማይገልጥ
ባለጠጋ ሆኖ ለድኻ የማይሰጥ
ድኻ ሆኖ መሥራት የሚጠላ ልቡ
ሦስት ፍሬ ቢሶች ለምንም አይረቡ።
ድኻ ሆኖ ዐመሉ ካለበት ቁም ነገር
ባንድ ኖት ይመስላል ዋጋው የሚከበር።
ከፍ ያለ ነውና የተሰጠው ስሙ
ማገልገሉ አይቀርም ሁል ጊዜ መጥቀሙ።
ትልቅ ሰው ተብሎ ምግባሩ ካልጠዳ
ስመ ቢስ ከሆነ ዐመለ ወራዳ
ወርቅ አንባር ይመስላል ቍሻሻና ዐፈር
ጥራጊ ጒድፍ ላይ ወድቆ የሚኖር።
ብዙዎቹ ተወልደው ከድኽነት ቦታ
በኋላም አግኝተው ይሆኑና ጌታ
ቶሎ ይረሱታል የጧቱን ለማታ
እየተሳናቸው መለስ ብለው ማየት
ማለዳ ሲነሡ የወጡበትን ቤት።
እንዳይነጋ እንዳይመሽ ብልኅት ተገኝቶ
ጊዜውን መከልከል እንዳይቻል ከቶ
እንዲሁም ባለም ላይ አለ ብዙ ነገር

በዚያም ቢሉት በዚህ መሆኑ የማይቀር።
ደስታና ሐዘን ውርጭና ፀሓይ
ሆነው ይመጣሉ በሰውነት ላይ
ሰው ደስ ባለው ጊዜ ሐዘኑን ይረሳል፤
ሐዘንም ሲያገኘው መጨነቅ ያበዛል።
አስቦ ሁለቱም አላፊ መሆኑን
ሲከፋው ደስታን፤ ደስ ሲለው ሐዘኑን
አስቦ በመጠን ሁሉን የወሰነ
ብልኅ ሰው ይባላል የተመሰገነ።
የሰው ገላ ለብሰን ሥጋን የመሰለ
ፍል ውሃ ሲነካው ቶሎ እየበሰለ
እንዴት ነጋም ጠባ ይጠጣል እሳት
አንዶ እሚቀቅል አልኮል የሚሉት።
ተገዢ ንወና ሰው ሁሉ ላመሉ፤
ሰካራም ሲሰማኝ ይለኛ ወደ ጅሉ።
መጠጥና ሴቶች የዋሉበት ስፍራ
ብዙ ሰው የፈጀ መሆኑ ነው ቁራ፤
የገባ ሰው ሁሉ እንደ ከብት ተነድቶ
አንዱም ሳይመለስ ቀረ ተበላሽቶ።
ከተንኰል አካሄድ ልቡናኽ የጠራ
በማንም ላይ ቢሆን ክፉ የማትሠራ
በመሆንኽን ዐውቀኸው ኅሊናኽ ሲኰራ
ያልደረሰበት ሰው እንዲያው በክፋት
ሊበድልኽ ቢሻ በጠላትነት
ለእንደዚኽ ያለ ጠብ መጨነቅኽ ቀርቶ
ኅሊናኽ ይታደስ በደስታ ሞልቶ።
ያላንዳች ምክንያት የተነሣው ዲና
ከግዜር ትልቅ ጸጋ ሊሰጥኽ ነውና።

ዐመፅና ወንጀል ዐድማም ሆነ ሤራ
ማንም ሰው አላየኝ ብለኽ ብትሠራ
ለማቅረብ የሚችል ክስና ወቀሣ
አንድ ሺ ምስክር መኖሩን አትርሳ።
ቢያሥቅም ቢያስለቅስም ቢገርምም ደስ ቢያሰኝ
ማንኛውም ይሁን አዲስ ነገር ሲገኝ
ዕጹብ ድንቅ እያለ ከዳር እስከ ዳር
ከጥንት የመጣ ነው ያለም መሸበር
ኋላ ግን ውሎ አድሮ ከርሞ በመሰንበት
ተርስቶ ይቀራል ሁሉም እንደ ዘበት።
ጋሬጣና አሽሟጣጭ አንድ ነው ባሕሪያቸው
የሚያስፈልገውን ሁሉ በመቦጨቃቸው።
ጋሬጣስ ቦጭቆም ያስቀራል በጥሶ፤
አሽሟጣች ከፉ ነው ይከተላል ነክሶ።
አጥፍቶ አሳዳቢ ዋሽቶ የሚረታ
ሰብሮ የሚያስከፍል ቀብጦ የሚያስመታ
ተማቶ የሚያሥቅ ተሳድቦ እሚቆጣ
ተበድሮ አስከፋይ ሰርቆ የሚያሳጣ
አስቀይሞ አኵራፊ አስለቅሶ አዛኝ
በድሎ የሚካስ ቀምቶ ተለማኝ
የሚታዘዝለት ሰው ሁሉ እንደ ሎሌ
አለ በያለበት አንዳንድ አፈ ጮሌ።
ጢስ ሳይኖረው እሳት ብቻውን አይነድም፤
እንዲያው ያለ ጥቅም ሰው አይዋደድም።
ሰውን ሰው ሲወደው አንድ ጥቅም አለው
መሠረት አድርጎ የሚከታተለው።
ደስታና ሐዘን ተስፋና ፍራት
የሰው ልጅ ዕድሜ ይዘው ያላባት

እየቈራረጡ ተከፋፈሏት።
ገና ነው እያሉ ካልሸፋፈኑት
ማን ሊያየው ይችላል ሞትን ፊት ለፊት?
ሕይወት እንደ አራስ ልጅ ዕድሜዋን ስትገፋ
አወዛውዙኝ ባይ ነች እስከታንቀላፋ።
ሲከተል ይኖራል ነገር ሸሺውን
አሽከር ባለቤቱን ጠፊም አጥፊውን።
ራብ በኽል ያልፋል ጊዜ በተረት፤
ጭንቅ በሣቅ ይረሳል ፍቅርም በወረት።
ሐሳቡን ሰመመን ወስዶ እየመለሰው
ቈይቶ ይነቃል የተታለለ ሰው።
ስንፍናን የዘራ ችጋርን ዐጨደ
ሲታረድ ይሥቃል ዋዛን የወደደ።
እጅግ ቢሽመግል ዓለም ምን ቢያረጅ
ይወዳል ጨዋታ እንደ ሕፃን ልጅ።
ቢሰፈር ቢቈጠር ቢገመት ቢለካ
እምዬ ውለታሽ አያልቅም ወይ ለካ!
እየተደረበ ሁለት ሰው ባንድ አካል
አንደበቱ ሲምል ልቡናው ይከዳል።
ገንዘብ ሰርገኛ ነው ሰው ሲያቀርብ ሰብስቦ
ድኽነት ግን ሲያርቅ ይመስላ ተስቦ።
ትምህርት ካልጨመረ በተፈጥሮ ዕውቀቱ
ሕፃን ልጅ ይሆናል ሰው፥ ከነሽበቱ።
በልቶ ማንቀላፋት ጠጥቶ መስከር
የሥራ ፈት ሙያ የሰነፍ ምግባር።
ከሐች ዓምናም ዓምና ካምናውም ዘንድሮ
እያስጠላኝ ሄደ የዚህ ዓለም ኑሮ።
የእግዚአብሔርን መኖር የሚክድ መንፈስ

ደን ያለ ሽፍታ ነው ዐዋጅ ለማፍረስ።
እሙን ወዳጅ የለም ባሕርይን የመሰለ
ይኖራል እስከ ሞት እንደ ተከተለ።
አይገኝም ከቶ ቢፈልጉ ዞሮ
መስማት ከማይፈልግ የባሰ ደንቈሮ።
ቢቈስልም ይድናል የተደበደበ፤
ምላስ ግን ይኖራል እንዳንገበገበ።
የሰው ነገር ብዝቶ በሆዴ ውስጥ ሞላ፤
ምን እንስሳ ልዋጥ ልቅም የሚበላ።
አጊጦ ሲያምርበት ዕውቀት በትሕትና
ኵራት አስጠየፈ ለብሶ ድንቍርና።
በሰው ልጅ ላይ ሳለ የቅናት በሽታ
ላንዱ ሐዘኑ ነው ያንደኛው ደስታ።
ፈላስፋው ሲመክር አደራ ብሏል
በምትሠራው ሥራ ቀስ ብለኽ ቸኵል።
ማዕርግ ለማግኘት ባለ ብዙ ክብር
በፊት ያስፈልጋል ተንቆ መኖር።
ምን ውብ ነገር ቢሆን ከማድነቅ በፊት
ይገባል ጭራሹን ቀድሞ መመልከት።

# የደስታና የሐዘን ቅልቅልነት።

ማን ሊያውቀው ይችላል
ያለምን ነገር፤
በጣም ይቸገራል
ባህሏን መናገር።
ሰው ባለው ጉልበቱ
የለፋበት ሥራ
ይቅርና ከንቱ
ፍሬ ሳያፈራ
ተስፋውም ተቋርጦ
ሐዘን ሲጫነው
መጥናናትን መርጦ
ቢንቅ መልካም ነው።
ልቡን በማጠንከር
ልቡን በማንጠር
መንፈሱ ሲጥናና
ተረስቶ የማይቀር
ሐዘን የለምና።
ለቅሶና ደስታ
ሳቅና ሐዘን
ያልተለዩ መንታ
በሆኑበት ቀን
ታየች ልትሰወር
ዓለም ተኽርጉርጉራ
የማይመረመር
ምስጢር ልታፈራ።
ደስታና ሐዘን
እየቀላቀልኩ

ልቤን ብዙ ዘመን
ስመግበው ኖርኩ።
ከፋኝም ደስ አለኝ
ብዩ ለመመለስ
መለየት አቅቶኝ
እስቲሳነኝ ድረስ
ዓለም ሌባ ሆና
ፍጥረቱ አታላይ
በክፋት ጐዳና
ተስማሙበት ወይ?
ዓለም በዚህ መንገድ
ወደ ጽልመት ጥላ
በፍጥነት ስትሄድ
አየናት በመላ።
አምራ እንደ ሰርገኛ
ለብሳ እየታየች
ሲቀርቧት ለቅሶኛ
ሆና ተገኘች።
እንባ እያፈሰሰች
እንደ ሬት መራራ
ዓለም ታለቅሳለች
በሥራችው ሥራ።
ምን አገኘሽ ብሎ
ለሚጠይቃት
ዐይኗ ኮከብ መስሎ
እንባዋም ውበት
ሥስቅ ታለቅሳለች
ምነው ማለታችሁ

አይችልም ትላለች
መለየት ዐይናችሁ
ዓለምን መውቀሡ
ይቅርብን ተነቅፏል
ሰው ሲሥቅ ማልቀሱ
መሆኑ ተጽፏል።

## ሁለት መላጦች።

ሁለት በራ ሰዎች ሲያልፉ በጐዳና
ዕቃ መሬት ወድቆ ብልጭ ሲል አዩና
ተሽቀዳድመው ሄደው ከቦታው ሲደርሱ
ተፎካከሩበት ሁለቱም ሊያነሡ።
በኋላም ተማተው በጥፊ በጡጫ
አንደኛው፥ ነተቀ በጉልበቱ ብልጫ።
አገላበጠና ቢመለከት ፈጥኖ
ዕቃውን አገኘው ማበጠሪያ ሆኖ።
እስቲ ሁላችሁም በሉ ፍረዱት
እሱ ራሱ፥ በራ ጠጉር፥ የለበት
ሮጦ፥ ተማቶ ቀምቶ ቢያመጣ
ምን ያደርግለታል ሚዶ ለመላጣ?
 ሰዎች ይፋጃሉ አስበው ሳይፈርዱ
 የተጣሉበትን ጥቅሙን ሳይረዱ፤
የከመጣላት በፊት ከመቀያየም
የነገሩን ፍሬ መረዳት መልካም።

# ለጸሓፊዎችና ለፈላስፎች ምስጋና።

የትምህርቱ እርሻ አለመጠን ሰፊ፤
ሑዳዱ መጽሐፍ ነው ገበሬውም ጸፊ
ሐሳብ ከሚባለው ከትልቅ ጐተራ
ብዕር እጅ ሆኖ ጨብጦ እየዘራ
የቀለሙን ፍሬ አብቦ እያፈራ
ለምልሞ ተገኘ መልካሙ አዝመራ።
እንዲህ ያለ አዝመራ እውነትም ትልቅ
ቢመረት ቢመረት ሰብሉ የማያልቅ
ሼክስፒር ሔን፥ ገት፥ ላፎንቴን፥ ሞሊዬር፥
እነ ቪክቶር፥ ኤቪል፥ ኤዞፕ፥ ኮርኔይና፥ ራሲን፤
በማርሼና፥ ኮፔ ቧሎና ላማርቲን
እነ ዶስቶዬቭስኪ ደግሞም እነ ፑሽኪን
ይህ መልካም አዝመራ እንዲገኝ ሲያግዙ
ተግተው አለድካም ሠርተዋል በብዙ።
ድካም ከማያውቁት ወደ ጐበዞቹ
እንመለስ ደግሞ ወደ ፈላስፎቹ።
ፕላቶና ዲዎገን ሶሎና ሶክራት
ማሌርብና ፖስካል፥ ባኮና ዴካርት
ቮልቴርና ሩሶ ዜኖ፥ ሄራክሊት
አንስቲቴኔ፥ አሪስቶት፥ እነ ዴሞክሪት
ያም፥ ሳይቀር ያም ሳይቀር እናንተ ሁላችሁ
ትጉህ ሠራተኞች የማታኪታችሁ
የሰው ልጅን መንፈስ አድርጋችሁ ሑዳድ
እያበጠራችሁ ስንዴውን ከንክርዳድ
ማሰብ በሚባለው ዶማ ቆፍራችሁ
ፍልስፍና እሚባል ወይን የተከላችሁ
ወይናችሁ አፍርቶ መደቡ ተስፋፋ፤

ብዙ ሰው እሸቱን እየበላ ፋፋ።
ብዙው ደረቁን ጠጅ ግሮ እየሰከረ
የሰማይ የምድሩን እየቀባጠረ
የሆነ ያልሆነ ነገር ተናገረ።
ለቀመሰው ሁሉ ጥንትም ሆነ ዛሬ
ጣዕሙ ይናገራል የወይናችሁ ፍሬ
ጠድቶ መገኘቱን ከመልካም ገበሬ።
ሁል ጊዜም ይልማ እንጂ መደቡ ይስፋፋ
ይህ መልካም ወይናችሁ ብዙ ሰው ያለፋ
ጠባቂ በማጣት አደራ እንዳይጠፋ።

# ለእመቤታችን ምስጋና።

ሰላም ላንቺ ይሁን ድንግል ማርያም፤
ሞልቶብሻልና ጸጋ በፍጹም፤
እግዜር ካንቺ ጋር አለ ለዘለዓለም።
ትበልጫለች አንቺ ከሴቶቹ ሁሉ፤
የሆድሽም ፍሬ ኢየሱስ በሙሉ
የተባረከ ነው በምድር በሰማይ፤
ቅድስት ያምላክ እናት እመቤቴ ሆይ
ሁል ጊዜ ልጅሽን ለምኝልን ለኛ
ለኅጢአተኞቹ ለሌለን መዳኛ።
በሞታችን ጊዜም ገሃነም ወራጅ
ከመሆን ሰውሪን ሁኝን አማላጅ።
ያዳም ልጆች ቤዛ
የኢየሱስ እናት
የገነት መዐዛ
የሙታን እምነት
ታሪክሽ ማማሩ

አንቺ የንጋት ኮከብ
ዝናውና ክብሩ
ተሰምቶ አይጠገብ።
ማዕበል ተነሥቶ
ዓለም ስትናወጥ
ሽብሩ በርክቶ
ፍጡርም ሲራወጥ
እጅሽን ዘርጊልን
አንቺ ሁኝኝ ተስፋ
ሞት እንዳያገኘኝ
ጨርሼ እንዳልጠፋ።
የለመነሽ በውነት
እምነቱ እየጠና
ሰውነቱን መቅሠፍት
አይነካውምና።
ያዳም ልጅ ሲሸበር
ትውልዱ ሊጠፋ
መና ሆኖ እንዳይቀር
አንቺ ሁኚው ተስፋ።
እግዜር ላገራችን
ቃል ኪዳን ሲገባ
ለኢዮጵያ እናታችን
ሆንሻት ባልደረባ።
ክፉ ቀን ሲመጣ
መዓት እየዘራ
ከሰዓቱ ቊጣ
ሰውሪያት አደራ።
የሃይማኖት ጳዳል

የሰማይ ንግሥት
የርኅራኄ አምሳል
የዓለም መድኀኒት
ጠላት በመጣ ቀን
ደግሞ እንዳትጠቃ
ቆመሽ ከሷ ወገን
ሁኘላት ጠበቃ።

## ጥልቅ አሳቦች።

ደጉንም ክፉንም ጨርሶ ያላየ
ከኢምንት ያልወጣ ካለም የተለየ
በያንዳንዱ አገር በያንዳንዱ ጐራ
በእያንዳንዱ ንብረት በእያንዳንዱ ስፍራ
እንደ ምን ያለ ግፍ እንዴት ያለ በደል
እንዴት ያለ ውርደት ሰው እንደሚቀበል
ስንቱን መጥፎ ነገር ቆሻሻ የገማ
ባይኖቹ ያላየ በጆሮው ያልሰማ
የሰዎችን ሐዘን የሰዎችን ለቅሶ
ተካፋይ ያልሆነ በፍጹም ጨርሶ
የመፈጠር ዕጣ ጽዋ ያልደረሰው
ምንኛ ተደለ ያልተወለደ ሰው!
አበባ ስታምር ቀለሟ ሲወዛ
ታበላሻታለች ጨካኝዋ ጥንዚዛ
ባንድ ሰው ላይ ሲያዩ አንድ መልካም ነገር
ምቀኞች በቶሎ ለማጥፋት ለማጥቁር
ተመልካችን ሁሉ ብላሽ ነው ሊያሰኙ
ተግተው ይሠራሉ እንቅልፍም አይተኙ።
አንድ ቤት ሲቃጠል እየተሯሯጡ

አይታችሁ ይሆናል ሰዎችን ሲወጡ።
ግራ ቀኝ አያዩም በሩጫ ሲሄዱ
ከድንጋጤ ብዛት ይመስላል ያብዱ።
ምሳሌ ፈልገን ጕዱን ብናወራው
እንደዚህ ያለ ነው ባለም የሚሥራው፤
ፍጹም እብድ መስሎ ይህ ሁሉ ያለም ሰው
በመውጣት በመውረድ የሚተራመሰው
የሚቅበዘበዘው ቸኵሎ እንደ ጕንዳን
ሁሉም ለጥቅሙ ነው ራሱን ለማዳን።
ባዘቅት ይመስላል የሰው ነፍስ ጠባይ
ጨለማ የሆነ ስሩ የማይታይ፤
በጥልቀቱ መጠን ወደ ታች ሲሰምጡ
ያላሰቡት ነገር ይገኛል በውስጡ።
አወይ ምኞት ምኞት ቁም ነገር ታላቁ!
ይንቅኽ ይሆናል ዋጋኽን ሳያውቁ
ለሚችኵልማ ገለባ ነኽ ባዶ
ግን ታጋሽ ለሆነ ሩቅ ማሰብ ለምዶ
መጪን ነገር አምኖ ለተመለከተ
ከሁሉም ከሁለም ትበልጣለህ አንተ።
ሊቆች ባንጎላቸው አንተን ያረገዙ
ጥበብን ወልደዋል አንድ አይደለም ብዙ።
ሁል ጊዜ ያፈራል ሰው እንደ ተመኘው፤
ምን ጥበብ ይገኛል ምኞት ያላገኘው።
ምኖት ያረገዘው አይቀርም በከንቱ፤
የሚወለድበት ይደርሳል ሰዓቱ።

# አዳምና በሬው።

ከወጣ በኋላ ከገነት ተሰዶ
አዳም ያርስ ነበር በሬዎቹን ጠምዶ።
አንዱ በሬ ቢቆም በከፋት ለግሞ
አዳም ደበደበው በዱላ ደጋግሞ።
በትር ቢበዛበት ያ በሬ ቢጨንቀው
ለምን ትማታለኽ? አለና ጠየቀው።
አልታዘዝ ስትል ምነው አትመታ
አለና መለሰ አዳም በቀጥታ።
በሬውም መለሰ እግዚአብሐኢር ደግ ነው፤
እሱ ነው መሓሪ ለፍጡር የሚያዝነው።
እሆናለሁ ብለኽ አንተም እንደ ጌታ
የበለስን ፍሬ የቀመስክ ለታ
ትእዛዙን ስታፈርስ ያንን ያኽል አዝኖ
አልደበደብኽም እንደዚህ ጨክኖ።
ይህንን ሲሰማ አዳም አለቀሰ፤
እግዚአብሔር አለው እየመላለሰ፤
አያልቅም ተገፍቶ አይ የኔን አበሳ
እንዴት ልችለው ነው ያለሙን ወቀሣ!
ቅጣቴ መች አንሶ ይዝለፈኝ እንስሳ!
በጣም አዘነና በዚህ የተነሣ
እሮሮ እንዳይሰማ አዳምን ሊረዳ
ከዚያን ቀን ዠምሮ አምላክ በመደዳ
እንስሳትን ሁሉ አደረገ ድዳ።



# ስለደራሲው በጥቂቱ

ከበደ ሚካኤል ጥቅምት 23 ቀን 1909 ዓ.ም በሰሜን ሸዋ -- ደብረ ብርሃን ከተማ አካባቢ ገርም ገብርኤል አጥቢያ ተወለዱ። በህፃንነታቸው የመጽሐፍ ቅዱስን ልዩ ልዩ ታሪኮች በወግ መልክ በመተረክ እንደ አነፅዋቸው የመሰከሩላቸው እናታቸው ወ/ሮ አፀደ ሚካኤል ጀንዲ እስከ ዘጠነኛ አመታቸው ድረስ በባህላዊን የግዕዝ ትምህርት እንዲቀስሙ እንዳስቻሏቸው ይነገራል። ከበደ በ1918 ዓ.ም ወደ አዲስ አበባ መጥተው በእናታቸው ወንድም በአቶ ሰይፉ ሚካኤል ልዩ ድጋፍ በ"አሊያንስ ፍራንሴስ" በፈረንሣይኛ የአንደኛ ደረጃ ትምህርታቸውን፥ በላዛሪስ ሚሲዮንም የመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን አጠናቀዋል።

ከበደ ሚካኤል እስከ ጣሊያን ወረራ ዋዜማ ድረስ በነበረው የተማሪነት እና የወጣትነት ቆይታቸው ከመደበኛ ትምህርታቸው ባሻገር በትርፍ ጊዜያቸው ልዩ ልዩ የፈረንሳይኛ መጻሐፍትን በማንበብ የቋንቋ የንግግር ችሎታቸውን አዳብረዋል። አንድም - በዘመናቸው ከነበሩት ቀደምት ታዋቂ ኢትዮጵያውያን ምሁራን - የአለቃ አፅመ ጊዮርጊስን፥ የአለቃ ኪዳነወልድ ክፍሌን፥ የፕሮፌሰር አፈወርቅ ገ/ኢየሱስን፥ የነጋድራስ ገብረ ሕይወት ባይከዳኝን እና የነቀኝ ጌታ ዮፍታሔ ንጉሴን አዳዲስ ሓሳቦች ቀስመዋል። ከትምህርት ቤት መምህራኖቻቸው ይሰጡዋቸው በነበረ ልዩ ድጋፎችም የግሪክን የሮማውያንን፥ የእንግሊዝን፥ የፈረንሳይን፥ የጀርመንን፥ የሩሲያን እና የኢታሊያን ፈላስፎች ጠቢባንና ሳይንቲስቶች "ታላላቅ ሰዎች" መጻህፍት አንብበዋል መርምረዋል።

ከኢጣሊያ ወረራ 1929 -1933 ዓ.ም በኋላ በ"ነፃነት መዝሙር" -የቅኔ መንገድ ልዩ ተሰጥኦዋቸውን አህዱ ያሉት ከበደ ሚካኤል ከሃገራችን ደራሲያን በላቀ መልኩ በዘመናዊ እሳቤና ሥነ ጽሑፋዊ ተሳትፎአቸው ከ16 በላይ የሚቆጠሩ ልዩ ልዩ የእውቀት ዘርፎች ፍልስፍና፥ ሥነመለኮት፥ ሥነ ትምህርት፥ ሥነምግባር፥ ሳይንስ፥ ሥነ ጥበባት፥ ቅኔ፥ ተውኔት "ብርሀነ ህሊና" በብእሮቻቸው መግለጫነት በአማርኛ፥ በፈረንሳይኛ፥ በእንግሊዝኛ፥ እና በጣሊያንኛ ቋንቋዎች ከ90 በላይ በታተሙ ከ200 በላይ ባልታተሙ ወጥና ትርጉም ድርሰቶቻቸው የኢትዮጵያን ዘመናዊ ሥነ ጽሑፍ አድማስ አስፍተዋል።

በአዳዲስ ሀሳቦች "አብራኄ ህሊና"ነት ሀዲስ ትውልድ ያፈሩት ፈላስማውና ባለቅኔው ከበደ ሚካኤል፥ ዘመናዊ ኢትዮጵያን ለማደራጀት በተደረገው ተጋድሎም በልዩ ልዩ የሚኒስትርነት ማእረጎች በግምባር ቀደምነት አገልግለዋል።

ፈላስፋ፥ ባለቅኔ፥ ፀሐፊ ተውኔት፥ ደራሲና አንጋፋው ጋዜጠኛ ከበደ ሚካኤል በአገራችን እንግዳና የመጀመሪያ የነበረውን የቀ.ኃ.ሥ. የ1957 ዓ.ም የሥነ ጽሑፍ ሽልማት በቀዳሚነት የተቀበሉ የ"ቀለም ሰው" ሲሆኑ፥ በዘላቂነት ሐዲስ ትውልድ ላፈራው የላቀ አስተዋፀኦዋቸውም የአ.አ.ዩኒቨርሲቲ ጥቅምት 26 ቀን 1990 ዓ.ም በሥነ ጽሑፍ የክብር ዶክትሬት ዲግሪ ሸልሟቸዋል።

ክቡር ደ/ር ከበደ ሚካኤል ኅዳር 3 ቀን 1991 ዓ.ም በ82 ዓመታቸው አረፉ። "ሰኔ 21 ቀን የከበደ ሚካኤል መታሰቢያ ቀን" ሆኖ ተሰይሟል።

## የደራሲው ሥራዎች።

1. የዕውቀት ብልጭታ (**ትምህርት**)
2. የመዠመሪያ እርምጃ (**ትምህርት**)
3. ታሪክና ምሳሌ ፫ኛ መጽሐፍ (**ትምህርት**)
4. ታላላቅ ሰዎች (**ትምህርት**)
5. የዓለም ታሪክ ፩ኛ ክፍል (**ትምህርት**)
6. ብርሃነ ኅሊና (**ግጥምና ቅኔ**)
7. የቅኔ አዝመራ (**ግጥምና ቅኔ**)
8. የቅኔ ውበት (**ግጥምና ቅኔ**)
9. ጃፓን እንደ ምን ሠለጠነች? (**ትምህርት**)
10. የትንቢት ቀጠሮ (**ቴአትር**)
11. አኒባል (**ቴአትር**)
12. በላይነህ/ የቅጣት ማዕበል (**ተውኔት**)
13. ዐፄ ካሌብ (**ቴአትር**)
14. አክአብ (**ቴአትር**)
15. ከይቅርታ በላይ (**ትምህርት**)
16. ሮሜዎና ዡልዬት (**ቴአትር**)
17. የቅጣት ማዕበል (**ቴአትር**)
18. ኢትዮጵያና ምዕራባዊ ሥልጣኔ
19. ትልቁ እስክንድር
20. ግርማዊነታቸው ባሜሪካ አገር
21. ሥልጣኔ ማለት ምንድነች? (**ትምህርት**)
22. የሥልጣኔ አየር (**ትምህርት**)
23. ቅዱስ ገብርኤል በምድረ ገነት (**ተውኔት**)

NIGUSS
DIGITAL LIBRARY